## ክፍል አንድ

## የዮሐንስ ወንጌልአንድምታ

### መግቢያ

ወንጌላዊ ዮሐንስ

የስሙ ትርጉም

ዮሐንስ የሚለው ስም የግሪክ ቃል ሲሆን "የሆሐናን" ወይም "ዮሐናን" ከሚለው የዕብራይስጥ ስም የተተረጎመ ወይም የተገኘ ነው። በእብራይስጥ "ዮሐናን" የሚለው ስም እግዚአብሔር ጸጋን አደረገ፣ ሰጠ፣ አጉናጸፈ በሚል ይተረጎማል በሐዲስ ኪዳን ዮሐንስ ተብለው የሚጠሩ የተወሰኑ ሰዎች ይገኛሉ።

ከእነዚህ ውስጥ የመጀመሪያውና በስፋት በወንጌላውያን የተጠቀሰው መጥምቁ ዮሐንስ ነው። ከመጥምቁ ውጪ ሌላው **ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ**ነው።

ሐዋ 12፡12-25፣ 13፡15፣13፡13፣ 15፡37 እንዲሁም የ4ኛ ወንጌል ጸሐፊ **የዘብዴዎስ ልጅ ዮሐንስ** ማቴ 4፡21፣ ማር 1፡19 ሉቃ 5፡10 የነጎድጓድ ልጆች ማር 3፡17

### የዮሐንስ ስሞች

- ✓ ጌታ የሚወደው ደቀ መዝሙር ዮሐ 19፡25-26
- ✓ ወልደ ነጎድጓድ
- ✓ ወልደ ዘብዴዎስ
- ✓ አቡቀለምሲል /ባለራዕይ
- ✓ ታኦጎሎስ/ታኦሎጎስ/ቴዎሎጎስ/ቴኦጎሎስ/ነባቤ መለኮት
- ✓ ወንጌላዊ



CS CamScanner

4ተኛውን ወንጌል የጻፈው ዮሐንስ ስለመሆኑ በወንጌሉ ውስጥ ግልጽ መረጃ ባለመኖሩ ጸሐፊው ዮሐንስ ነው የሚለው በብዙዎች ዘንድ ሳያስማማ ቆይቷል፡፡ነገር ግን ምንም እንኳ ስሙ በግልጽ ዮሐንስ ተብሎ ባይጠቀስም ኢየሱስ ይወደው የነበረው ደቀ መዝሙር 4ተኛውን ወንጌል የጻፈው የዘብዴዎስ ልጅ ዮሐንስ ሊሆን እንደሚችል ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ ዮሐ 21:24 ከቤተክርስቲያን አባቶች መካከል ሄሬኔዎስ/ኢሬናዎስ (Irenaeus 130-200 ዓ.ም) የዘብዴዎስ ልጅና ተወዳጁ ደቀ መዝሙር እንደ አንድ ሰው አድርጎ በመግለጽና በማረጋገጥ አስተምሯል፡፡ የእስክንድርያው ቀሌምንጦስ (150-215) ዮሐንስ በተማሪዎቹና በወዳጆቹ ጥያቄ መሠረት በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ በእውነትና በተጨባጭ መረጃ የተሞላ መንፈሳዊ የሆነ ወንጌል ጻፈ በማለት እንደመሰከረ ሊቃውንት ይገልጻሉ፡፡

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የመጽሐፉን ይዘት፣ የአጻጻፍ ስልቱን፣ ጸሐፊው የተጠቀመበትን ቋንቋ፣ በመጽሐፉ ውስጥ የተገለጹትን የባህልና ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች፣ ድርጊቶቹ የተከናወኑበትን ጊዜያትና ቦታ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ጥናት ካደረገች በኋላ ጸሐፊው "ተወዳጁ ደቀ መዝሙር" ተብሎ የተጠራው የዘብዴዎስ ልጅ ዮሐንስ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ደርሳለች፡፡ በእኛ ትውፊት ደግሞ በወንጌሉ መጀመሪያ ላይ ብሥራተ አብ ትሩፍ ረድዕ ተናጋሪ በመለኮት ዮሐንስ ወልደ ዘብዴዎስ ፍቁረ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ አሐዱ እም አሠርቱ ወክልዔቱ ሐዋርያት ጸሎቱ ወበረከቱ-----የሚል አርእስት ተጽፎ እናገኛል፡፡

## ወንጌሉ የተጻፈበት ቦታ

ምንም እንኳ ወንጌሉ ውስጥ ግልጽ የሆነ መረጃ ባይኖርም ታሪካዊ የሆኑ ጽሑፎችንና የቤተክርስቲያን አባቶች ከሰጡት ምስክርነት በመነሣት ሊቃውንት ወንጌሉ ሊጻፍ የሚችልበትን ቦታ በተመለከተ የተለያየ አስተያየት ይሰጣሉ፡፡ የተወሰኑት እንደሚከተሉት ይሆናል

### እስክንድርያ

የዮሐንስ ወንጌል በግብጻውያን ዘንድ ለጽሑፍ ሥራ በስፋት ይጠቀሙበት በነበረው በፓፒረ[ስ] ተጽፎ ከ140-200 ዓ.ም ስለተገኘ ወንጌሉ እስክንድርያ ውስጥ ሊጻፍ እንደሚችል የሚገልጸ[ው] ሊቃውንት አሉ፡፡



CamScanner

## አንጾኪያ

አግናጥዮስ ስለ ዮሐንስ ወንጌላዊ የመሰከረና ወንጌሉ ውስጥ የተገለጹትን ዓበይት ትምህርቶች እየጠቀሰ ያስተማረ በመሆኑ እንዲሁም ከወንጌሉ በተጨማሪ በዮሐንስ እንደተጻፈ ስለሚታመኑት መልእክቶቹም ሆነ ራዕይ በቂ መረጃ እንደነበረው ከጽሑፎቹ መረዳት ይቻላል።

በነዚህ ምክንያቶች አግናጥዮስ ይህን ሁሉ መረጃ ሊያገኝ የቻለው ዮሐንስ በኖረበት አከባቢ በአንጾኪያ ስለኖረ ይሆናል። ዮሐንስ አንጾኪያ ውስጥ ስለኖረ እዚያው ሆኖ ሊጽፈው እንደሚችል ሊቃውንት መላ ይመታሉ።

## ኤፌሶን

ወንጌሉ የተጻፈበትን ቦታ በተመለከተ በስፋት ተቀባይነት ያገኘው ግን ኤፌሶን የሚለው ነው። ኤፌሶን በታናሽ እስያ (በዛሬቱ ቱርክ) ውስጥ የምትገኝ ከተማ ናት። ሄሬኔዎስ/ኢሬናዎስ የሰጠው ምስክርነት ተጠቃሽ ነው። የጌታ ሐዋርያት ከነበሩት መካከል አንዱ የሆነውን ዮሐንስ ኤፌሶን በመሆን ጻፈ ይላል። Raymond E.Brown (2003)

## ወንጌሉ የተጻፈበት ጊዜ

ወንጌሉ የተጻፈበትን ጊዜ ለማወቅ ሊቃውንት ብዙ ጥናት ቢያደርጉም መቼ እንደተጻፈ በትክክል ለመወሰን አልተቻለም። ወንጌሉ ውስጥ የተገለጹት ውስጣዊ መረጃዎችንና ተጨማሪ የሆኑ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ምስክርነትን እንዲሁም የታሪክ መዛግብት ውስጥ የተገኙ ፍንጮችና የሊቃውንት አስተያየት

- ወንጌሉ ከ70-90 ዓ.ም እንደተጻፈ የሚገምቱ አሉ። ምክንያቱም በአይሁዳውያን መካከል ጥላቻና ልዩነት እየሰፋ መምጣቱን ወንጌሉ ስለሚገልጽ፣
- በመጀመሪያው ክ/ዘመን መጨረሻ ከ90-100
- በተጨማሪም ወንጌሉ ስለ ኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ መፍረስ (70 ዓ.ም) ምንም ዓይነት ስለማይናገር ወንጌሉ የተጻፈው ከ70 ዓመት በፊትመሆን አለበት ብለው የሚያምኑ አሉ።በእኛ ትውፊት ጌታ ባረገ በ30/35 ዓመት ኔሮን ቄሣር በነገሠበ7/8 ዓመት እንደተጻፈ በቅድመ ወንጌል ላይ ተገልጻል።

4. ቅዱሳት መጻሕፍት የሚሰጡት ምስክርነት(ዮሐ.5፡39-46)
5. የመጥምቁ ዮሐንስ ምስክርነት(ዮሐ.1፡7፤5፡35)
6. የሐዋርያት ምስክርነት (ዮሐ.1527፤19፡35)
7. የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት(የሐ.15፡26፤16፡13-14) ናቸው ። ሌላው ደግሞ እኔ በማለት የሚገልጻቸው7ነገሮች አሉ።እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ(6፡35)፣እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ(8፡12)፣እኔ የበጎች መግቢያ ነኝ(10፡7)፣መልካም እረኛ እኔ ነኝ(10፡11)፣ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ(11፡25)፤እኔ መንገድ እውነት ሕይወት ነኝ(14፡6)፣እኔ የወይን ግንድ ነኝ የሚሉት ናቸው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያከናወናቸው ተአምራት ሰባት ናቸው

1. በገሊላ ቃና ውኃውን ወደ ወይን መለወጡ፣(2፡1-12)
2. የመኮንኑን ልጅ መፈወሱ ፣ (4፡46)
3. መጻጉዕን መፈውሱ ፣(5፡1-25 )
4. በረከተ ኅብስት ፣(6፡5)
5. በባሕር ላይ መራመዱ፣ (6፡16)
6. ዕውር ሆኖ የተወለደውን ዓይን ማብራቱ ፣(9፡1)
7. አልአዛርን ከአራት ቀን በኋላ ከሞት ማስነሣቱ (11፡1)በተመሳሳይ መልኩ 3 ቁጥርን ወይም አንድን ነገርለሦስት ጊዜ ያህል ደጋግሞ በመግለጽ መልእክት ያስተላልፋል። ከነዚህም ውስጥ 3 የፋሲካ በዓላት ፣3 የመጥምቁ ዮሐንስ ምስክርነት፣ኢየሱስ 3 ጊዜ እንደተፈረደበት ፣ጴጥሮስ 3 ጊዜ እንደካደው ፣ጌታ ጴጥሮስን 3 ጊዜ ትወደኛለህ ያለው ይገኝበታል።

   ሌላው በወንጌሉ አጻጻፍ ሂደት ላይጥንድ እና ከአንድ በላይ ትርጓሜ ሊኖራቸው የሚችሉ ቃላቶች መጠቀሙ ለየት ያደርገዋል።ለምሳሌ ብርሃንና ጨለማ፣እውነትና ሐሰት ፣ ሕይወትና ሞት፣ውሃና የሕይወት ውሃ፣ብርሃንና እውነተኛ ብርሃን ፣እንጀራና የሕይወት እንጀራ የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል።

   **የወንጌሉ ጥንቅር**

## ምዕራፍ አንድ

**የቃል ቀዳማዊነት/አካላዊነት ፣ሕይወትነት፣ብርሃንነት**

**ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ**

በመጀመሪያ ቃል ነበረ 1፡1

‹መጀመሪያ ነበረ›ሲል ይህ መጀመሪያ መቼ ነው የምንስ መጀመሪያ ነው ጀማሪውስ ማነውየሚሉት ጥያቄዎች ይነሣሉ በአጠቃላይ የጊዜ ጉዳይ ሳይሆን ከጊዜ ውጪ በሆነ መልኩ ‹የመሆን ወይም የመኖር ነገር ነው። ‹ከመጀመሪያ ነበረ›የሚለው እና ‹ቃል ነበረ› የሚለው አገባብ በአብ ህልው ሆኖ ከዘለዓለም የሚኖር መሆኑን የሚስረዳ ነው ። ይህንን ቃል ለሰው ሰጥተን የተረዳነው ከሆነ ፍጥረታዊውን ጊዜ የሚያሳይ ነው ። እግዚአብሔርን በሚመለከት ቃሉን ስንጠቀምበት የሚያመለክተን ጥንት የሌለው መሆኑን ነው። ስለዚህ ነበረ የሚለውን የእኛንተፈጥሮ መሠረት አድርገን ስንረዳው የሚያመለክተን ያለፈውንና ፍጻሜ ያለውን ጊዜ ነው።አስቀድሞና ኋላ የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ጊዜን ነው ። ለእሱ ፍጥረታዊ የሆነ ጊዜ የለውም ።ለእግዚአብሔር አብና ለወልድ መጀመሪያ የሚለውንቃል ስንጠቀም ዘመን በማይቆጠርለት አኗኗር ከዘለዓለም የነበሩ ያሉመሆናቸውን እንረዳለን።

በመጀመሪያ ቃል ነበረ ሲል በቅድምና የነበረ ነውማለት ነው።አንድም፣ቀዳሚሁ ለፍጥረት ሲል ነውከጥንተ ፍጥረት አስቀድሞ የነበረ ነው፣አንድም አካላዊ ነው ሲል ነው።ቃል ሲባል ከአንደበት እንደሚወጣ ዝርውቃል አይደለም። አካላዊና ፍጹመ አካል ነውእንጂ።

__ዝርዋን ቃላት__

- አአትሪኮን፡- በአየር የሚፈስው ቃላችን ነው።(ኢሳ.6፡3፣ራዕ.4፤8)
- ቦሪፎሪኮን፡-ነቢያት ከእግዚአብሔር የሰሙት ቃል ነው። (ዘጸ19፡3፣33፡1-2፣ዘኁ.28፡1፣ሕዝ.18፡1)
- አተርጋዎን፡-የመላእክት ቃል ነው። /1ቆሮ13/ ፣ (ሃይ.አበ ጎርጎርዮስ ክፍል21 ም.13፡23)



CamScanner

## ስለ ሦስት ነገር ቃል ብሎታል

- ቅድምናን
- ህልውናን ለመንገር፣ለመግለጽ
- ፈጠረበት ለማለት

**ህልውና**

ከልብና ከእስትንፋስ ተለይቶ የሚገኝ ቃል የለም።ማለት ቃል ከልብና ከእስትንፋስ የሚለይበት ጊዜ የለም ።ወልድም በአብ ህልው ሆኖ ለሰዓለም ይኖራል። ‹እመኑ ከመ አነ በአብ ወአብ ብየ› እኔ በአብ አብ በእኔ ህልው እንደሆነ እመኑ ነው።(ዮሐ 14:11)

ህልዋን እሙንቱ በአብ እንዘ ይሄልዩ በበአካላቲሆሙ ነአምን በአብ ከመ ህልው በወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፣ወነአምን በወልድ ከመ ህልው በአብ ወመንፈስ ቅዱስ፣ ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ ከመህልው በአብ ወወልድ እንዲል(ዮሐ.ሊቀጳ ዘእስክንድርያ ሃይ. አበ. ክፍል 1:10-11)

**ቅድምና**

ልብና እስትንፋስ ቀድመውት ወደ ኋላ የሚገኝ ቃል የለም ።ልብና እስትንፋስ ከቃል የሚቀድሙበት ጊዜ የለም ። አብም ከወልድ የቀደመበት ጊዜ የለም ወይም አብ ከቃል ውጪ የኖረበት ጊዜ የለም ።ቃልም ያልነበረበት ጊዜ የለም ። ስለዚህ ቃል የሥላሴ ቅድምናን ያስረዳል አሐቲ ቅድምናሆሙ ለሥላሴ ወዕሩያን እሙንቱ በቅድምና እንዲል (ኪራኮስዘእንጾ.ሃይ.አበ.ክፍል1:5)

**ፈጠረበት ለማለት**

ፍጥረታት የተፈጠሩት በወልድ ቃልነት ነው ። ዓለም በእግዚአብሔር ቃል እንደተፈጠረ እናውቃለን (ዕብ.11:3)

**ለምን ቃል አለው**

አምላክ ቢለው አማልክት በዘጸጋየተባሉ አሉ መዝ.81:6 ወልድም ቢለው እስራኤልን ወልድየ ዘበኩርየ ይላቸዋል እንዲሁም ምእመናን በጸጋ የሚወለዱት ልደት አለና ያሻማል ስለዚህ በማያሻማ ቃል ቃል አለው።



CamScanner

ሌላው ወልድ የሁለቱን አንድነት (የአብና የወልድን) ያስረዳል እንጂ የሦስቱን አንድነት አያስረዳም ቃል ግን የሦስቱን አንድነት ያስረዳል ። ቃለ አብ ወቃለ መንፈስ ቅዱስ ፣ወልድኒ ቃሎሙ ለአብ ወለመንፈስ ቅዱስ እንዲል(አቡሊዲስ ሃይ.አበ.ገጽ138 ክፍል2፡8-9) የሦስቱን አንድነት የሚያስረዳ እዱ፣መገዘራዕቱ፣ የማኑ ለምን አላለውም ያልን እንደሆነ ይህ አፍአዊ ሦስትነታቸውን እንጂ ውሳጣዊ አንድነታቸውን አያስረዳም ። ውሳጣዊ አንድነታቸውን የሚያስረዳ ጥበቡ፣ ምክሩ ኀሊናሁም አላለውም ለምን ቢባል **የጥበብ ፣የምክር ፣የኅሊና መዲናቸው መገለጫቸው ቃል ስለሆነ ቃል አለው።አንድም** ቃ ል ከልብ ተገኝቶ በልብ ህልው ሆኖ ሲኖር ልገለጽ ባለ ጊዜ በቃል እንዲገለጽ ወልድም ከአብ ተገኝቶ በአብ ህልው ሆኖ ሲኖር ልገለጽ ባለ ጊዜ በሥጋ ተገልጣልና **አንድም** ለምሳሌ እንዲመቸው ነው ለቃል አርምሞ ጽርአት የለውም፤ አይቋረጥም ፤በልብ ውስጥ ይወጣል፤ ይወርዳል ጸሐፊ ሲጽፍ ረቂቁ ቃል ከልቡና ሳይለይ በቀለም ገዝፎ እንዲታይ አካላዊ ቃልም ከአብ አንድነት ሳይለይ በሥጋ ገዝፎ ታይቷልና ። ‹ቀዳሚሁ ቃል› ባለው ኀደረ በብእሲ የሚል ሳምሳጢ ጳውሎስ፣ ለፌ እማርያም ክዋኔሁ ለወልድ የሚሉ እነ ፎጢኖስ ተረተውበታል።

<u>ሳምሳጢ ጳውሎስ</u> የተወለደው በታናሽ እስያ በሶርያ አካባቢ ነው። የነበረበትም ዘመን በ3ኛ መቶ ክ/ዘመን ነው ሳምሳጢ የተባለውም በሀገረ ስብከቱ ስም ነው የጳውሎስ ሳምሳጢ ክህደት ዳይናሚስቲክ ሞናርኪያሊዝም ይባላል።

**ቃል አካል ሳይኖረው** በአብ አካል ውስጥ የኖረ ኃይል ነው ይላልና።

በእሱ አስተሳሰብ ቃል ከሥጋዌ በፊት አካል አልነበረውም። በአብ ህልውና የሚኖር ዝርው ቃል፣ ዝርው ኃይል ነው እንጂ <u>ለምሳሌ</u> በሰው ጭንቅላት ንባብ፣ አእምሮ እንደሚኖሩ፣ ይኸም **ምሥጢረ ሥላሴን** ማፍለስ ስለሆነ አንድ አካል አንድ ገጽ ካለው ከሰባልዮስ ክህደት ጋር አንድ ነው።

<u>በምስጢረ ሥጋዌም</u>ከማርያም የተወለደው ዕሩቅ ብእሲ ነው ስሙም ኢየሱስ ይባላል። ዕሩቅ ብእሲ ኢየሱስ በዮርዳኖስ በተጠመቀ ጊዜ በአብ ህልውና ውስጥ የነበረው ዝርው ቃል መጥቶ አደረበት ከዚያ በኋላ ራሱ ባደረገው ተጋድሎና በሠራው ትሩፋት በጸጋ የእግዚአብሔር ልጅ ለመባል በቃ።

በመስቀል ላይ ስለታየውም አምላካዊ መግቦት ሲናገር ዝርው ቃል የሚለው ወልደ እግዚአብሔር እስከ መከራ መስቀል ድረስ ዕሩቅ ብእሲ ከሚለው ከማርያም ልጅ ከኢየሱስ ጋር አብሮት ኖረ። ዕሩቅ ብእሲ የማርያም ልጅ ኢየሱስ በተሰቀለ ጊዜ ዝርው ቃል ወልደ እግዚአብሔር ተለይቶት ሄደ ይላል።

ጳውሎስ ሳምሳጢ ከግኖስቲኮች በወሰደው የኅድረት ትምህርቱ የቃልን በቅድምና መኖር ኋላም በሥጋ በመገለጥ መምጣቱን፤ በአማናዊ ተዋሕዶ ሰው መሆኑን ፤ሥጋ መልበሱን ስለ ካደ በ268 ዓ.ም በአንጾኪያ ጉባኤ ተድርጎ እሱም ትምህርቱም ተወግዘዋል።

## ፎጢኖስ

ፎጢኖስ በ4ተኛው መቶ ክ/ዘመን የነበረ ሲሆን የጳውሎስ ሳምሳጢ የኅድረት ትምህርትን በማደስ ወልድ ወይም ቃል በአካል የተገለጠው ከማርያም በተወለደ ጊዜ ነው ብሏል። ለፌ እማርያም ክዋኔሁ ለወልድ ይህም አባባል የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እንደሚያመሰጥሩት ልጅ በአባቱ አብራክ ህልው ሆኖ ቆይቶ ሰው ሆኖ እንዲወለድ ማለት ነው።

**ወውእቱ ቃል ኀበ እግዚአብሔር**

ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ።

በቅድምናም ነበረ ያልሁት ያቃል በእግዚአብሔር አብ ህልው ነው። ህልውናውም ብርሃን በክበብ (በቅርፅ) ፤ነበልባል በእሳት፤ ርጥበት በስፋሐት፤ ቃል በልብ ህልው ሆኖ እንደሚኖረው ዓይነት ነው። ህልዋን እሙንቱ በአብ---

ቃልም በእግዚብሔር ዘንድ ነበረ በሚለው መዓርገ ርቀት የሚሰጡ እነ አቡሊናርዮስ፤ መዓርገ ርቀት የሚሰጡ እነ አርጌንስ አንድ ገጽ የሚል ሰባልዮስ ተረትተውበታል።

## አርጌንስ

አርጌንስ የተወለደው 185 ዓ.ም በእስክንድርያ ነው። አባቱ ሊዊኒዳስ አንበሳ ይባላል። አርጌንስ የመጀመሪያ ትምህርቱን የተማረው በእስክንድርያ ት/ቤት ሲሆን በትምህርት ኮትኩቶ ያሳደገው ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ ነው። አርጌንስ በሙያው በንጽሕናውና በመንኖ ጥሪት

የታወቀና የተደነቀ ነበር። በ17 ዓመቱ በመምህሩ እግር ተተክቶ በእስክንድርያ ት/ቤት ለ30 ዓመታት ያህል ሲያስተምር ኖሯል። የ25 ዓመት ወጣት እያለ ከሥራው ጎን ለጎን የፍልስፋና ትምህርትን ከአሞንዮስ ሳካ ተምሯል። አርጌንስ ብዙ መጻሕፍት ጽፏል። ብዙ ደቀ መዛሙርትንም አውጥቷል።

የአርጌንስ የትርጓሜ ትምህርት ምሥጢርን እንጂ ዘይቤን አይመለከትም ነበር። ፍልስፍናን ከክርስትና እምነትን ከእወቀት ጋር ለማስታረቅ የሞከረ ነበር።

የአርጌንስ የምስጢረ ሥላሴ ትምህርት እንደ መምህሩ እንደ ቀሌምንጦስ የተዘበራረቀና የተምታታ ነበር። በመጀመሪያ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ወልድ አብን በመልክ የሚመስል በባሕርይ የሚተካከል አካላዊ ነው።

ወልድ ከአብ ቢወለድም አብ አይቀድመውም ለምሳሌ ‹‹ወልድየ አንተ ወአነ ዮም ወለድኩከ›› ያለውን ሲተረጎም ‹‹ዮም›› የሚለው በእግዚአብሔር ዘንድ ዘለዓለም ማለት ነው። በእግዚአብሔር ዘንድ መዓልትና ሌሊት ሠርክና ነግህ የለምና። የወልድም ቀዳማዊ ልደት ዘመን አይቆጠርለትም። ቀዳሚም የለውም እያለ ያስተምራል።

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ይህን ሁሉ ንዶና አፈራርሶ መዓርገ መንግሥት እያበላለጠ በተዋረድ ይናገራል። ለምሳሌም ከአብ ጋር በባሕርይ አንድ ነው ያለውን ያንኑ ወልድን እንደገና ከአብ ያሳንሰዋል አካለቢስ፣ ዝርው ኃይል፣ ዝርው ጥበብ ነው ይለዋል።

ስለ ሥራው ሲናገር አብ ዓለምን ለመፍጠር የሚገለገልበት መሣሪያ ወይም መለኪያ ነው ይለዋል። በማዕርግና በደረጃም ደግሞ ሁለተኛው እግዚአብሔር እያለ ይጠራዋል። የአርዮስ አስተሳሰብ ምንጩ ይኸ ነው።

ወልድ የአብ ተወራጅ ነው መንፈስ ቅዱስ ደግሞ የወልድተወራጅ ነው ወይም አብ ከወልድ ይበልጣል ወልድም ከመንፈስ ቅዱስ ይበልጣል ይል ነበር። በሞተ በ299 ዓመቱ በ553 ዓ.ም በቀዳማዊ ጁስቲያን ዘመን መንግሥት ቁንስጥንጥንያ በተደረገው ጉባኤ አርጌንስ ከነመጻሕፍቱ አወግዟል።

## ሰባልዮስ

ሰባልዮስ በ3ኛው መቶ ክ/ዘመን የነበረ የሊቢያ ሰው ነው። በትምህርት ምክንያት ወደ ሮም ሄደ። በዚያም እግዚአብሔር አንድ አካል አንድ ገጽ ነው የሚለውን ትምህርት ተማረ ይህን የተማረው ‹‹አብ መከራ ተቀበለ›› ከሚሉ መናፍቃን ነው። አብ ብሉይ ኪዳን ስለሠራ ‹‹አብ ተባለ›› በዘመነ ሥጋዌ ሰው ሆኖ ሥጋ ለብሶ ስለ ታየ ሐዲስ ኪዳንንም ስለ ሠራ ‹‹ወልድ ተባለ›› ኋላም በበዓለ ጰራቅሊጦስ በአምሳለ እሳት ወርዶ ለሐዋርያት ምሥጢር በመግለጹ ቋንቋ በመናገሩ ‹‹መንፈስ ቅዱስ ተባለ›› እንጂ አንድ አካል አንድ ገጽ ነው ብሏል። ስለዚህ ቃል አካል አለው ሲል ይረታል።

### ወእግዚአብሔር ውእቱ ቃል

ያቃል እግዚአብሔር ነው።ማለት በተለየ አካሉ ፈጥሮ የሚገዛ ነው። በዚህም ቃል ምትሐት ውላጤ የሚሉ እነማኒእነ ዋሊጦስ፣ ዝርው የሚሉ እነመርቅያን፣ ወልድ ፍጡር በመለኮቱ የሚል አርዮስ ተረተውበታል።

### ማኒ

በግኖስቲክ ትምህርት የታወቀው ማኒ የፋርስ ተወላጅ ነው። በእርሱ ፍልስፍና የመነናውያን እንቅስቃሴ ተመሠረተ። ማኒ በ216 ዓ.ም በፋርስ ከሚኖሩ የጠንቋይ ቤተሰብ ተወለደ የዞራስተር የምንታዌ ትምህርትና ፍልስፍና አጠና ኋላም ክርስትናን ተቀበልኩብሎ ተጠመቀ ለቅስና ማዕረግም ደርሶ ነበር። ነገር ግን ለሐዋርያት ትምህርት ታማኝ ባለመሆኑ ከቤተ ክርስቲያን ተወግደ። በ242 ዓ.ም በሻፑር ዘመን ‹‹ጰራቅሊጦስ ነኝ›› እያለ ያስተምር ጀመር። በ276 ዓ.ም ሞተ። የማኒ ትምህርት ከግኖስቲኮች ትምህርት ጋር አንድ ነው። ብዙ ምትሐትና ጥንቆላም አለበት።

በማኒ ትምህርት መሠረት ሁለት አማልክት አሉ አንዱ ረቂቅ ሁለተኛው ግዙፍ ናቸው። ስለ ሰው ተፈጥሮ ሲናገር ደግሞ ሰው ሁለት ነፍሳት አሉት። አንዱ ሥጋዊትና ግዙፍ ስትሆን የክፋት ምንጭ ናት። ሌላዋ ደግሞ ደግና ብርሃናዊት ናት። በማኒ አስተሳሰብ ይህችን ብርሃናዊት ነፍስ ከክፉዋና ከግዙፏ ነፍስ ለመታደግ ኢየሱስ መስሎ (በምትሐት) ወደዚህ ዓለም መጣ። የሰዎች ነፍሳትም ከዚህ ግዙፉ ዓለም ተላቀው ወደ ደጉና መልካሙ አምላክ የሚደርሱበትን መንገድ አስተማራቸው። ሆኖም ኢየሱስ ሥራውን ሳይፈጽም በመሄዱ ጅምሩን



CamScanner

## ሰባልዮስ

ሰባልዮስ በ3ኛው መቶ ክ/ዘመን የነበረ የሊቢያ ሰው ነው። በትምህርት ምክንያት ወደ ሮም ሄደ። በዚያም እግዚአብሔር አንድ አካል አንድ ገጽ ነው የሚለውን ትምህርት ተማረ ይህን የተማረው ‹‹አብ መከራ ተቀበለ›› ከሚሉ መናፍቃን ነው። አብ ብሉይ ኪዳን ስለሠራ ‹‹አብ ተባለ›› በዘመነ ሥጋዌ ሰው ሆኖ ሥጋ ለብሶ ስለ ታየ ሐዲስ ኪዳንንም ስለ ሠራ ‹‹ወልድ ተባለ›› ኋላም በበዓለ ጰራቅሊጦስ በአምሳለ እሳት ወርዶ ለሐዋርያት ምሥጢር በመግለጹ ቋንቋ በመናገሩ ‹‹መንፈስ ቅዱስ ተባለ›› እንጂ አንድ አካል አንድ ገጽ ነው ብሏል። ስለዚህ ቃል አካል አለው ሲል ይረታል።

### ወእግዚአብሔር ውእቱ ቃል

ያቃል እግዚአብሔር ነው።ማለት በተለየ አካሉ ፈጥሮ የሚገዛ ነው። በዚህም ቃል ምትሐት ውላጤ የሚሉ እነማኒእነ ዋሊጦስ፣ ዝርው የሚሉ እነመርቅያን፣ ወልድ ፍጡር በመለኮቱ የሚል አርዮስ ተረተውበታል።

### ማኒ

በግኖስቲክ ትምህርት የታወቀው ማኒ የፋርስ ተወላጅ ነው። በእርሱ ፍልስፍና የመነናውያን እንቅስቃሴ ተመሠረተ። ማኒ በ216 ዓ.ም በፋርስ ከሚኖሩ የጠንቋይ ቤተሰብ ተወልደ የዞራስተር የምንታዌ ትምህርትና ፍልስፍና አጠና ኋላም ክርስትናን ተቀበልኩብሎ ተጠመቀ ለቅስና ማዕረግም ደርሶ ነበር። ነገር ግን ለሐዋርያት ትምህርት ታማኝ ባለመሆኑ ከቤተ ክርስቲያን ተወግደ። በ242 ዓ.ም በሻፑር ዘመን ‹‹ጰራቅሊጦስ ነኝ›› እያለ ያስተምር ጀመር። በ276 ዓ.ም ሞተ። የማኒ ትምህርት ከግኖስቲኮች ትምህርት ጋር አንድ ነው። ብዙ ምትሐትና ጥንቆላም አለበት።

በማኒ ትምህርት መሠረት ሁለት አማልክት አሉ አንዱ ረቂቅ ሁለተኛው ግዙፍ ናቸው። ስለ ሰው ተፈጥሮ ሲናገር ደግሞ ሰው ሁለት ነፍሳት አሉት። አንዱ ሥጋዊትና ግዙፍ ስትሆን የክፋት ምንጭ ናት። ሌላዋ ደግሞ ደግና ብርሃናዊት ናት። በማኒ አስተሳሰብ ይህችን ብርሃናዊት ነፍስ ከክፉዋና ከግዙፏ ነፍስ ለመታደግ ኢየሱስ መስሎ (በምትሐት) ወደዚህ ዓለም መጣ። የሰዎች ነፍሳትም ከዚህ ግዙፉ ዓለም ተላቀው ወደ ደጉና መልካሙ አምላክ የሚደርሱበትን መንገድ አስተማራቸው። ሆኖም ኢየሱስ ሥራውን ሳይፈጽም በመሄዱ ጅምሩን



CamScanner

ለመፈጸም ለሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን በመጠኑ ላከላቸው። በ277 ዓ.ም በንጉሡ በቤሕራም ቀዳማዊ ትእዛዝ በስቅላት ተቀጥቶ ሞተ።

## መርቅያን

መርቅያን ከታናሽ እስያ ግኖስቲኮች ቀንደኛው መርቅያን የተባለው ነው። መርቅያን ፓንዱበምትባል የታናሽ እስያ ግዛት ውስጥ የተወለደ ነው። አባቱ ኤጲስቆጶስ ነበር። በወጣትነቱ በቤተክርስቲያን ጥፋት ስለፈጸመ አባቱ ከሀገረ ስብከቱ አስወገደው መርቅያን የክርስቶስን ሰው መሆንና ሥጋ መልበስ በምትሐት እንጂ አማናዊ ነው አይልም ክርስቶስ የተቀበለው መከራ መስቀልም በምትሐት ስለሆነ እሱን አላገኘውም ባይ ነው። የመርቅያን ትምህርት ከ4ተኛው መቶ ክ.ዘ ጀምሮ እየቀዘቀዘ በ6ኛው መቶ ክ.ዘ ጨርሶ ጠፋ።

## አርዮስ

አርዮስ በ3ኛው መቶ ክ.ዘ አጋማሽ ላይ በ257 ዓ.ም ገደማ በአፍሪካ ሰሜን ክፍል በተገኘው በሊብያ ተወለደ ከቤተክርስቲያን ጋር ያጣላውን ትምህርት ያገኘው በአንጾኪያ ትርጓሜ ትምህርት ቤት ከሉቅያኖስ ነው።

አርዮስ የሚነገርለት እግዚአብሔር ፈጣሪነት እንጅ ወላዲነት የለውም። እሱ እንደሚለው ቀዳሚ የሌለው አብ ብቻ ነው። ከእሱ በቀር ሁሉም የተፈጠረ ነው። በአርዮስ አመለካከት መውለድና መፍጠር ሞክሼ ቃላት ናቸው እንጂ የተለያየ ትርጉም የላቸውም።

በምሥጢረ ሥላሴም አብ አባት ተብሎ የተጠራውና በአባትነት የታወቀው ከዘመናት በኋላ እንጂ ከዘመናት በፊት አብ አይባልም ነበር። ይላል በህልውናው ውስጥ ‹‹ጥበብና ቃል›› የሚባሉ ኃይላት ነበሩ። ከእነዚህ ሌላ ደግሞ እግዚአብሔር በራሱ ፈቃድ ዓለምን ለመፍጠር ስላሰበ መሥፈሪያና መለኪያ እንዲሆነው ሌላ ጥበብ ፈጠረ። አንጥረኛ መዶሻውን፣ ሸክላ ሠሪ መደቧን አስቀድማ እንድትሠራ ከፍጥረተዓለም ጥቂት ቀደም ብሎ የተፈጠረው ይህ ጥበብ በተፈጥሮ ያገኘው አካልና ህላዌ አለው። በመጽሐፍ ቅዱስም ጥበብ፣ ቃል፣ ወልድ፣ አርአያ እየተባለ ይጠራል። በባሕርይ ፍጡር ስለሆነ ያልነበረበት ጊዜ ነበር ከመፈጠሩም በፊት አልነበረም። ባሕርዩም ፍጹም ስላልሆነ የአብን አካላዊ ባሕርይ ለማየትም ለማወቅም አይቻልም።

በፈቃደ እግዚአብሔር ከእምነት ከዓለማት በፊት የተፈጠረ ነውና፡፡ ፍጡር እንደመሆኑ ውላጤ የባሕርዩ ነው፡፡ ‹‹ማዘን፣ መተከዝ፣ መደሰት፣ መበሳጨት›› ሰው መሆንም ራሱ በአርዮስ ግምት የባሕርዩን ተወራጅነት ያመለክታል፡፡ ቃል ሰው ለመሆን የመጣው ቃሉ የመታዘዝ ግብር ቢኖርበት ነው ይላል፡፡ ታዲያ እንደዚህ ያለውን የባሕርይ አምላክ ማለት እንዴት ይቻላል ይላል፡፡ እሱም ትምህርቱም በኒቅያ ጉባኤ በ325 ዓ.ም ተወግዟል፡፡

## ወከማሁ ቀዳሚሁ እምቀዲሙ ኀበ እግዚአብሔር ውእቱ

ያቃል በእግዚአብሔር አብ ህልው ነው እንዳልኩ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ህልው ነው፡፡ እንድም ወገንቱ ቀዳሚሁ እምቀዲሙ ይላል፡፡ ይህ ቃል ከጥንት ጀምሮ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ህልው ነው፡፡ በዚህም ቃል መንፈስ ቅዱስ ሕጹጽ የሚሉ እነ መቅዶንዮስ ተረተውበታል፡፡

## መቅዶንዮስ

መቅዶንዮስ ከቅድስት ሥላሴ ሦስተኛው አካል መንፈስ ቅዱስ ሕጹጽ ፍጡር ነው ብሏል፡፡ ያን ጊዜ የቁስጥጥንያ ንጉሥ የነበረው ቴዎደስዮስ ቀዳማዊ በቁስጥጥንያ ጉባኤ እንዲደረግ ለቤተክርስቲያን አባቶች መልእክት አስተላለፈ 150 ሊቃውንት ተሰብስበዋል፡፡ የዚህ ጉባኤ ሊቃነ መናብርት ብዙ ጊዜ ተለዋውጠዋል፡፡ መጀመሪያ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ነበር፡፡ ሁለተኛ ኔክታሪዎስ ነበር፡፡ ሦስተኛ ጢምቴዎስ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ኢሳ 6፡3 ቅ.ቅ.ቅ እግዚአብሔር ጸባኦት እያሉ ሲያመሰግኑ የሰማቸውመላእክት የሥላሴን አንድ አምላክነት የአካልን ዕሪና የባሕርይን አንድነት መመስከራቸው መሆኑን ገልጻል፡፡ ጌታ ‹‹በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ ሲል አንድ አምላክ ናቸው እንጂ የሚበላለጡ አለመሆናቸውን ገልጾ ተናግሯል፡፡ ከዚህ በኋላ መቅዶንዮስን አውግዘዋል፡፡

መቅዶንዮስ ሁለት ጊዜ የቁስጥንጥንያ ፓትሪያርክ ሆኖ ተሹሟል፡፡ የክህደት ትምህርቱ ቀደም ብሎ በ362 ዓ.ም በሮም ጉባኤ ተወግዟል፡፡ ይህ ጉዳይ ለሁለተኛው የቁስጥንጥንያ ጉባኤ ቀርቦ የመቅዶንዮስን ትምህርት በአንድ ድምፅ አውግዞታል፡፡

ቀዳሚሁ ቃል ባለው በቀዳሚ ኮነ ቃል ይላልእስመ ውእቱ ይቤ ወኮነ ካለው ጋር ንባብ ቢያስተባብራቸው (ቢያመሳስላቸውም) ምስጢር አያስተባብራቸውም፡ እኒያነ ተፈጠሩ ሲል ነው እርሱን ግን በቅድምና ነበረ ሲለው ነውና፡፡ በቀዳሚ ኮነ ቃል ባለው በቀዳሚ ሀሎ ቃል ይላል



CamScanner

በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ ያለውን ንባብ ቢያስተባብራቸው ምስጢር አያስተባብራቸውም። እኒያነን በቀዳማይ ዕለት በቀዳማይ ሰዓት ተፈጠሩ ሲል ነውጥንት አላቸው ጥንታቸው ዕለተ እሑድ ናት።እሱን ግን በቅድምና ነበረ ሲለው ነውና ። እግዚአብሔር ብሎ ሦስትነታቸውን ተናገረ አንስ ሰበ እቤ እብል እግዚአብሔር በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እንዲል (ባስልዮስ ዘአንጾ ሃይ.አበ.ገጽ420 ክፍል1:6) አንድም ኀበ፣ኀበ ብሎ ሦስትነታቸውን እግዚአብሔር እግዚአብሔር ብሎ አንድነታቸውን ተናገረ ሊቃውንት ይህን መሠረት በማድረግ ስለ ምስጢረ ሥላሴ በስፋትና በጥልቀት ተናግረዋል።

## ምሥጢረ ሥላሴ

እግዚብሔር በስም፣ በአካል፣ በግብር ሦስት በመለኮት፣በባሕርይ፣በህልውና፣በአገዛዝ፣በሥልጣን፣በፈቃድ አንድ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍትና የቤተክርስቲያን አባቶች ምስክርነት በቂ ማስረጃ ነው።

### ምሥጢረ ሥላሴ በብሉይ

‹ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ› ዘፍ.1:26 ንግበር የሚለው ብዛትን ማለትም ከአንድ በላይ መሆኑን ግሱ ያመለክታል። አርአያነ አምሳሊነ አንድነትን ይገልጻል። እንዲሁም ይቤ እግዚአብሔር ንዑ ንረድ ወንክዓው ነገሮሙ ለከለዳውያን ዘፍ.11:6-8 ንዑ ንረድ የሚለው ከአንድ በላይ መሆኑን ሲያመለክት ይቤ እግዚአብሔር የሚለው አንድነትን ይገልጻል። አነ ውእቱ አምላከ አብርሃም ወአምላከ ይስሐቅ ወአምላከ ያዕቆብ ዘጸ.3:6 አምላክ፣አምላክ፣አምላክ ሲል ሦስትነታቸውን አነ ውእቱ የሚለው አንድነታቸውን ያስረዳል። ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ ሣህሉ ለእግዚአብሔር መልዐ ምድረ ወበቃለ እግዚአብሔር ጸንዐ ሰማያት ወእምእስትንፋሰ አፉሁ ኩሉ ኃይሎሙ ይላል።መዝ.32:6 ሣህሉ ለእግዚአብሔር አብ ፣ ቃለ እግዚአብሔር ወልድ፣እስተንፋሰ አፉሁ መንፈስ ቅዱስ ነው። ነቢዩ ኢሳይያስም ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት ፍጹም ምሉዕሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ ኢሳ.6:3 ቅዱስ ፣ቅዱስ፣ ቅዱስ ሦስትነታቸውን ስብሐቲከ የሚለው አንድነታቸውን ያስረዳል።

### ምስጢረ ሥላሴ በሐዲስ ኪዳን

ምሥጢረ ሥላሴ ከብሉይ ኪዳን በኃላ መልኩ በሐዲስኪዳን እግዚአብሔር በስም፣ በአካል፣በግብር ሦስት በመለኮት፣በባሕርይ አንድ መሆኑ ተገልጻል። በጥምቀትና በዮርዳኖስ አብ

በደመና መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወልድ በሥጋ ማርያም መገለጹ ትልቅ ማረጋገጫ ነው። ማቴ.3፡17 ፣ማር.1፡9-11፣ ሉቃ.3፡21፣ማቴ 17፡1-17 እንዲሁም መልአኩ በሉቃስ ወንጌል መንፈስ እግዚአብሔር ቅዱስ ይመጽእ ላእሌኪ ወኃይለ ልዑል ይጼልለኪ ሲል (ሉቃ. 1፡32-34) መንፈስ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፣ኃይለ ልዑል ወልድ፣ልዑል አብ መሆኑን መረዳት እንችላለን። ራሱ ባለቤቱም ወእንዘ ታጠምቅዎሙ በሉ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ማለቱ ሦስቱ አካላት በስም መገለጻቸውንና የስም ሦስትነታቸውን ያስረዳናል። (ማቴ.28፡19) ቅዱስ ጳውሎስ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ፣የእግዚአብሔር ፍቅርየመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን 2ቆሮ13-14

## ምሥጢረ ሥላሴ በሊቃውንት

‹አምላክ ውእቱ አብ አምላክ ውእቱ ወልድ አምላክ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ወኢይትበሀሉ ሠለስተ አማልክተአላ አሐዱ ውእቱ እሙንቱ› (አትና. ዘእስክ. ሃይ.አበ. ገጽ74 ክፍል1፡4)‹ሥላሴ በተዋሕዶ ወተዋሕዶ በሥላሴ ተጋብአ በተከፍሎ ተከፍሎ በተጋብኦኅቡራን እንበለ ተሌልዮ ወሊሉያን እንበለ ትድምርት›()‹እንዘ አሐዱ ሠለስቱ ወእንዘ ሠለስቱ አሐዱ›እንዳለ ቅዱስባስልዮስ ዘቂሣርያ ‹ይሤለሱ በአካላት ወይትዋሐዱ በመለኮት› እንዳሉሠለስቱ ምእት

‹ነአምን በአብ ከመ ህልው በወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፣ወነአምን በወልድ ከመ ህልው በአብ ወመንፈስ ቅዱስ፣ ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ ከመህልው በአብ ወወልድ› እንዲል (ዮሐ.ሊ.ቀጳ ዘእስክንድርያ ሃይ. አበ. ክፍል 1፡10-11)

## ‹ዘቦቱ ኩሉ ኮነ› ሁሉ በእርሱ ሆነ

ሁሉ በእርሱ ህልውና፣ በእርሱ ቃልነት፣ በእርሱ አንድነት ተፈጠረ **ወዘእንበሌሁሰ አልቦ ዘኮነ ወኢምንትኒ** ከተፈጠረው ፍጥረት ግን ያለ እርሱ ህልውና፣ ቃልነት፣ አንድነት ምንም ምን የተፈጠረ የለም። በሐልዮ በአርምሞ የተፈጠረውን አብ በነቢብ በገቢር የተፈጠረውን ወልድ ፈጠረ የሚሉ አሉና በአርዮስም ያሳይበታል። አርዮስ ፈጥሮ ፈጠረበት ካለ እርሱን(ወልድን) በማን ፈጠረበት ያሰኝበታልና። ወንጌላዊው ያለ ወልድ ምንምን የተፈጠረ የለም ካለ ይህቃል የወልድን ፈጣሪት ያስረዳናል።በዚህ መሠረት ወልድ/ቃል ከአብ ጋር በባሕርይ ፣በመለኮት አንድ በሆነ ሥልጣን የዓለማት ፈጣሪ ነው እግዚአብሔር ነው፣ አምላክ ነው ስለዚህ ወልድ ያልነበረበት ጊዜ እንደሌለ ዘለዓለማዊናባሕርያዊ ተረክቦ ያለው ለዘለዓለም ከአብ ጋር በህልውና

የሚኖር እንደሆነ እንረዳለን ። በዚህ ቃል ወልድ ፍጡር የሚል አርዮስ ይረታበታል።**በእርሱ ሕይወት ነበረች፣ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች**

በእርሱ ሲል በቃል ውስጥ ሕይወት ነበረች ማለት ነው ። እርሱ የሕይወት መገኛ ሕይወትን የሚሰጥ ነው። (5፡25፣1፡28) ፣እኔ መንገድ እውነት ሕይወት ነኝ(14፡6)፣እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ (6፡35)

**ብርሃን የተባለውም እርሱ ነው።** ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛ ብርሃን (ከብርሃን የተገኘ ብርሃን) ፣እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ (10፡12) ብርሃን ሆኖ መምጣቱንሲገልጽ ነው። የአብንና የወልድን ሕልውናቸውን ለመግለጽ ወልድን ብርሃነ ጽድቅ የእውነት/የባሕርይ ብርሃን በሚል ኃይለ ቃል ገለጸው።ብርሃን ተገኘ በሚባልበት ጊዜ ከብርሃን የተወለደ ብርሃን ቅደም ተከተል በሌለበት ጊዜ ልክ በዚያች የጊዜ ተረክቦ አንድ ላይ እንደሚገኝ ሁሉ ወልድም ምን ጊዜም በዘለዓለማዊነት ከአብ ጋር በሕልውና አንድነት መኖሩና ዓለም ከመፈጠሩ በፊትም ቅደም ተከተል ሳይኖርበት እንደ አባቱ ቀዳማዊ ሆኖ በዘለዓለማዊ ቅድምና መኖሩን ያሳየናል።

**በዓለም ነበረዓለሙም በእርሱ ሆነ**

መጣ ብሎ ነበርና በዓለሙ የሌለ ሆኖ አይደለም በዓለም ምሉዕ ነውሀሉ ብሎ ነበርና በዓለም ነበረ ማለት ዓለም ይወስነዋል ማለት አይደለም ከዓለም በአፍአ ነውማለት ምሉዕ ነው። **ወዓለምሰ ኢያእመሮ ዓለሙ ግን አላወቀውም**

ላይኛው ዓለም ሌላ ይህ ዓለም ሌላ ነው ይህ ዓለም አላወቀውም ዕውቅና አልሰጠውም በዓለም ተቀባይነት አላገኘምአንድም አላመኑበትም ማለት ነው ዐውቀውትስ ቢሆኑ የክብርን ጌታ ባለሰቀሉትም ነበር (1ቆሮ.2፡8)

**የእግዚአብሔር ልጆች**

ያመኑበት የተቀበሉት ከእግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ/በሃይማኖት ከእግዚአብሔር ተወለዱ የእግዚብሔር ልጅ የመባል ሥልጣንን አገኙ።

***ቃል ሥጋ ኮነ ወኅደረ ላዕሌነ።*** *ቃል ሥጋ* ኾነ ጸጋንና እውነትን ተመልቶ በእኛ ላይ አደረ፣ ኾነና አደረ (ኮነና ኅደረ) የሚሉት ግሦች ለነገረ ድኅነት ወሳኝ ነገሮች ናቸው። *ሥጋ* ኾነና አደረን ለየብቻ ተነጣጥለውም የምንጠቀማቸው ከኾነ ትክክለኛውን ትርጉም አይሰጡም። ኾነ



CamScanner

ለብቻው ሲሆን ውላጤን፣ ኅደረ ደግሞ ለብቻው ሲሆን ኅደረትን ይፈጥራል። ነገር ግን አንዱ የአንዱ ጠባቂ ከኾነና ተደጋግፎ ከኾነ ትክክለኛውን የነገረ ሥጋዌ ትርጉምን ይሰጠናል። የግእዝ በግእዝ ትርጓሜ **ቃል ሥጋ ኾነ** ማለት ሥጋን ነሣ ማለት ነው። ሥጋን ነሣ ማለትም የሰውን መልክ ያዘ ማለት ነው ብሎ ተርጉሞታል። በቅድምና የነበረ አካላዊ ቃል ሥጋ ሆነ። ቃል ከሥጋ ተዋሐደ ማለት ነው።

**ተዋሕዶውም** ዘእንበለ ፍልጠት (ያለመለያየት)፣ ዘእንበለ ቱሳሔ (ያለመቀላቀል ያለመደባለቅ)፣ ዘእንበለ ውላጤ (ያለመለወጥ)፣ ዘእንበለ ትድምርት (ያለመደራረብ) ነው።

መለኮት ከሥጋ፣ ሥጋ ከመለኮት ጋር በአካል እንዴት ተዋሐደ

- የመለኮት አካል በሥጋ አካል ሳይለወጥ የሥጋ አካል በመለኮት አካል ሳይለወጥ፣
- የመለኮት አካል ከሥጋ አካል ጋር ሳይቀላቀል፣ ሳይለያይ፣ ሳይከፈል፣ የሥጋ አካል ከመለኮት አካል ጋር ሳይቀላቀል፣ ሳይለያይ፣ ሳይከፈል። በመዋሐድ (በተዋሕዶ) አንድ አካል ኾነ።

መለኮት ከሥጋ፣ ሥጋ ከመለኮት ጋር <u>በባሕርይ</u> እንዴት ተዋሕደ?

- የመለኮት ባሕርይ በሥጋ ባሕርይ ሳይለወጥ፣ የሥጋ ባሕርይ በመለኮት ባሕርይ ሳይለወጥ።
- የመለኮት ባሕርይ ከሥጋ ባሕርይ ጋር ሳይቀላቀል፣ ሥጋ ባሕርይ ከመለኮት ባሕርይ ጋር ሳይቀላቀል፣ ሳይከፈል በመዋሐድ (በተዋሕዶ) አንድ ባሕርይ ኾነ። ስለዚህ አንድ አካል ባሕርይ ኾነ ማለት ነው።

<u>**ቃል ሥጋ ኾነ**</u> ማለት ቃል ወደ ሥጋነት ተለወጠ ማለት አይደለም። ለምሳሌ የቃና ውሃ ተለውጦ ወይን እንደኾነው የሎጥ ሚስት ተለውጣ ጨው እንደ ኾነችው ዓይነት አይደለም። (ዘፍ.19፡26)

ቃል ሥጋ ኾነ ሲባል ሥጋን ብቻ ለበሰ ተዋሐደ ማለት አይደለም ሥጋ ኾነ የሚለው ሰው መሆኑን አቡሊናርዮስ ሥጋ ኾነ የሚለውን ይዞ ነፍስን አልነሣም/አልተዋሐደም በነፍሱ ቦታ መለኮቱ ኾነው ይላል። ነገር ግን ቅዱስ መጽሐፍ ሥጋ የሚለው ነፍስ የተለየውን ሥጋ/በድን አይደለም። ሥጋን ብቻ ቢዋሐድ ኖሮ ሰው ሥጋው እንጂ ነፍሱ አልዳነችም ማለት ነው። ነፍስን እንደነሣ ብዙ የቅዱሳት መጽሕፍት ምስክርነቶች አሉ። ለምሳሌ እስመ ሞቱ እስ



CamScanner

የሐሥሥዋ ለነፍስ ዝ ሕጻን፣ የሕጻኑን ነፍስ የሚልዋት ሞተዋልና (ማቴ 2፡19)፡፡ አባ አመኀጽን ነፍስየ ውስተ እዴከ አባት ሆይ ነፍሴን አደራ (ማቴ 27፡ 50)፡፡ መጽሐፍ ነፍስን ሥጋ፣ ሥጋን ነፍስ በማለት ይጠራል/ይናገራል

**__ለምሳሌ__**፡- ኢትቅትል ነፍሰ ሲል ትርጉሙ ነፍስ አትግደል ማለት ሲሆን በቀጥታ ትርጉሙ ከተመለከትነው ትርጉም አይሰጠንም ነፍስ አትሞትም አትገደልምና "አትፍርህዎሙኬ ለእለ ይቀትሉ ሥጋከሙ ወለነፍስከሙኒ ኢይክሉ ቀቲሎታ" ሥጋችሁን የሚገድሉትን አትፍሩ፡፡ ነፍሳችሁን መግደል አይቻላቸውምና (ማቴ 10፡32)፡፡ ይላል ስለዚህ ነፍስን በሥጋ መጥራቱ ነው፡፡ በመጽሐፈ ኪዳን ርእዮ ሞት እንዘ ይወርድ በሥጋ፣ ሞት ዲያብሎስ ጌታ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ሲወርድ አይቶ ሲል ነፍስን ሥጋ በማለት መጥራቱ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ቃል ሥጋ ኾነ ማለትም ነፍስ የተለየው ሥጋን ሳይሆን ፍጹም ሰው ኾነ ማለት እንደ ሆነ ከዚህ መገንዘብ እንችላለን፡፡

**በእኛም አደረ** ሲል ላእሌነ ማለቱ ሥጋ በቅድምና ነበረ ባሕርዩን አግዝፎ ታየ ለሚሉት መናፍቃን ምላሽ እንዲሆናቸው ነው በጽርዕ ደግሞ ወበውስቴትነ ይላል፡፡ ይህ ደግሞ ነፍስ አልነሣም እንደመስኖ ውሃ እንደ ማድጋ ውሃ ገብቶ ወጣ ለሚሉት መናፍቃን ምላሽ እንዲሆናቸው ነው፡፡ በአጠቃላይ ላዕሌነ ወበውስቴትነ የሚለው ነፍስንም ሥጋንም እንደተዋሐደ ለማስረዳት ነው፡፡

**"ወርኢነ ስብሐቲሁ ከመስብሐተ አሐዱ ዋሕድ ለአቡሁ"** ለአባቱ እንደ አንድ ልጅ የሚሆን ክብሩን አየንለት ለአባቱ አንድ የኾነ ልጅ የአባቱ ገንዘብ ሁሉ ገንዘቡ ነው፡፡ ለወልድም የአብ ገንዘብ፣ ገንዘቡ ነውና እስመ ኩሉ ዘቦ ለአቡየ ዚአየ ውእቱ አባቴ ያለው (ጥ) ሁሉ የእኔ ነው (ዮሐ.14፡) አንድም ስብሐቲሁ ለዋሕድ ነው፡፡ እንደ አንድነቱ ያለ ክብሩን አየንለት አንድም ስብሐት ያለው ተአምራቱን ነው አባቱ በኤልያስ አድሮ አንድ ምውት፣ በኤልሳዕ አድሮ ሁለት ምውት እንዳስነሣ እሱም ሰው ሆኖ ሥጋ ለብሶ የዕለት ሬሣ ወልደ መበለትን፣ ወለተ ኢያ ኤሮስን፣ የአራት ቀን ሬሣ አልዓዛርን ሲያስነሣ አየነው፡፡ አንድም አባቱ በሙሴ ላይ ብርሃን ሲስል እንደ አየን እሱም በደረቅ ግንባር ዓይንን ሲፈጥር አየን የብሉዩን ለአብ የሐዲሱን ለውልድ ሰጥቶ መናገር ልማድ ስለሆነ እንጂ በሁሉም አሉበት፡፡ ዮሐንስ በብሉይ የት ነበርና አየነው አለ ቢሉ፡፡ በብሉይ የነሙሴን ዓይን፣ዓይን አድርጎ ነው፡፡

**ዘምሉዕ ጸጋ** ጸጋን የተመላ፣ ጸጋ ያለው የባሕርይ ክብሩን ነው። ለሰው የጸጋ አድርጎ የሚሰጠው ስለሆነ፣

<u>**ጸጋ በዲ በጸጋ**</u>፡ በመንፈስ ረድኤት ላይ መንፈስ ልደትን፣ በኦሪት ላይ ወንጌልን፣ በአእምሮ ጠባይ ላይ አእምሮ መንፈሳዊ ተቀበልን።

**ለእግዚአብሔርሰ አልቦ ዘርእዮ ግሙራ** እግዚአብሔርንስ ከቶ በባሕርዩ ያየው የለም። ባባቱ ዕሪና ያለ ወልድ በባሕርዩ አይቶ ነገረን እንጂ። አንድም ከነቢያት ወገን ልጅ ሆኖ ያየው የለም። ልጁ ልጅ ሆኖ በባሕርዩ አይቶ ነገረን እንጂ።

**የዮሐንስ መጥምቅ ምስክርነት**

- ዮሐንስን ክርስቶስ ነህ ቢሉት አይደለሁም አለ እንጂ ነኝ አላለም።
- ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ አስቀድሞ የነበረው ነው፤ ማለት የባሕርይ አምላክ ነው።
- ነዋ በግዑ ዘየአትት ኃጢአተ ዓለም የዓለምን ኃጢአት የሚያስተሠርይ የእግዚአብሔር በግ እነሆ አለ።

  **እኔ ግን አላውቀውም** ማለት ቃል ተጨዋውቶ፣ መማለጃ በልቶ፣ ተዘምዶተ ሥጋ ይዞት አድልቶ ይሉኛል ብሎ አንድም የዮሐንስ አስተዳደግ በገዳም፣ ጌታ ግን በዓለም ነውና። አንድም ካንድ ቀን በቀር አየረቶት ስለላወቀ፣
  መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ሲቀመጥበት አየሁ ብሎ መስከረ።
  **የመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት**
  ዮሐንስ ነዋ በግዑ ብሎ ሲመሰክር ሰምተው ጌታን ከተከተሉት ከሁለቱ ደቀመዛሙርት አንዱ የስምኦን ጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ ነው። የእርሱን (የዮሐንስን) ሳናገር ቀረን ስለ ትሕትና ነው። እንድርያስና ዮሐንስ የዮሐንስ መጥምቅ ደቀ መዛሙርት ናቸውና። እንድርያስም አስቀድሞ ወንድሙ ስምኦንን አገኘ። ረከብናሁ **ለመሲሕ** ዘይብልዎ **ክርስቶስ** የተባለ መሲሕን አገኘነው።
  ክርስቶስ ቃሉ የግሪክ ሲሆን በዐረቡ መሲሕ በግእዙ ቅቡዕ የተቀባ ማለት ነው ይህም ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ማለት ነው። ክርስቶስ የሚለው የተዋሕዶ ስም ነው እንጂ የመለኮት ብቻ ወይም የትስብእት ብቻ አይደለም የሥግው ቃል ስም ነው በግእዝ ቅቡዕ የተቀባ ሲል ነገሥታት፣ ካህናት እንደሚቀቡት ያለ ቅብዐት አይደለም። ይኸም አምላክ ሰው ቢሆን የወጣለት ስም ነው። ወገ ስም



CamScanner

ዘውእቱ ክርስቶስ ወፍካሬሁ ቅብዐት ምስለ አምጣነ ትስብእቱ ረከቦ ለዋሕድ እንዲል ከበረ መባሉም በሥጋ ነው። ወይም ተቀባ የምንለውም መለኮት ከሥጋ ጋር በተዋሕደ ቅጽበት ሥጋ የባሕርይ አምላክ መሆኑን፣ የሥጋ ገንዘብ ለቃል የቃል ገንዘብ ለሥጋ መሆኑን ነው ። ስለዚህ ሲዋሐድም ሲቀባም አንድ ጊዜ ከመ ቅጽበተ ዓይን ነው። ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ይዞት ሄደ። ጌታም ባየው ጊዜ የዮና ልጅ ስምኦን አንተ ነህ አለው። አንተ ኬፋ ትባላለህ ኬፋ በእብራይስጥ፣ ጴጥሮስ በበጽርዕ፣ ኰኵሕ በዐረብ፣ በግእዝ ዕብን ይባላል።

**ፊልጶስና ናትናኤል**

ፊልጶስም ናትናኤልን አገኘ መሳሳብ ሆነ።  ረከብናሁ ለኢየሱስ  ዘይብልዎ ወልደ ዮሴፍ ዘጸሐፈ ሙሴ በውስተ ኦሪት ወነቢያት ተነበዩ በእንቲአሁ፤ ሙሴ በኦሪት፣ የጻፈለትን፣ ነቢያትም ትንቢት የተናገሩለትን የዮሴፍን ልጅ የናዝሬቱን ኢየሱስን አግኝተነዋል። ላዋቂ አነጋገር ነው። አንድም አይሁድ የዮሴፍ ልጅ የሚሉትን የናዝሬቱን ኢየሱስን አግኝተነዋል። ናትናኤልም በውኑ ከናዝሬት ደግ ሰው ይገኝ ዘንድ ይቻላልን አለው። መሆኑንንም አለመሆኑንም  መጥተህ እይ ናትናኤል ምሁረ ኦሪት ነው። ፊልጶስ ተከራክሮ ማስረዳት ባይቻለው፣ ኢየሱስም  ናትናኤልን ወደሱ ሲመጣ አየውና በእውነት ከዳት ተንኮል የለሌለበት እስራኤላዊ እነሆ ብሎ ስለእርሱ ተናገረ። ናትናኤልም ወዴት ታውቀኛለህን አለው። ጌታም ፊልጶስ ሳይጠራህ  በፊት ከበለስ በታች ሳለህ አየሁህ አለው።

- ሄሮድስ ሕጻናትን ባስገደለ ጊዜ እናቱ ከበለስ ሥር ሠውራው ነበርና ያን ጊዜ ያዳንኩህ እኔ ነኝ ሲል፣
- ሰወው ገድሎ የጎልማሳ ሚስት ቀምቶ የማይገባ ሥራ ሲሠራ ነበርና ይህን ስታደርግ አውቅብሃለሁ ሲል፣
- ምሁረ ኦሪት ነውና የተነገረው ትንቢት ደረሰ የተቆጠረው ሱባኤ ቀረ ኤለ ነበርና አውቅልሃለሁ ሲለው ነው።
- የበለስ ቅጠሉ ሰፋፊ እንደሆነ ኃጢአት ሰፍናብህ ገናብ አየሁህ ሲለው ነው።

ናትናኤልም መምህር ሆይ በእነት አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ የእስራኤልም ንጉሣቸው አንተ ነህ አለው። ጌታም ከእፀ በለስ ሥር አየሁህ ብልህ አመንክን እንግዲህ ወዲህ ከዚህ የበለጠ ታያለህ አለው። ሦስት ዓመት ከሦስት ወር የሚደረገውን ተአምራት አንድም ዕውቀቱ ከሌዋውያን ካህናት ከምድራውያን ነገሥታት እንዲበልት

ለማጠየቅ ፣ ለማያት ሲከፈቱ የእግዚአብሔር መላእክት ወደ ወልደ እጓለ እመሕያው ክርስቶስ ሲወጡ ሲወርዱ ታያላችሁ ብየ በእውነት እነግራችኋለሁ። ሰማ አከፈትም አይዘጋም ያልተገለጠ ምስጢር ተገለጠ ሲል ነው። መላእክት ጌታ ሰው ከመሆኑ አስቀድሞ ሰው የጸለየውን ጸሎት ያቀረበውን መሥዋዕት ለማሳረግ አወጡም አይወርዱም ነበር። ሰው ከሆነ ወዲህ ግን የሚወጡ የሚወርዱ ሆነዋል። አንድም አምላክ ሰው ሆነ ፣ ሰው አምላክ ሆነ እያሉ ርዕደቱን ዕርገቱን ለመንገር የሚወጡ የሚወርዱ ሆነዋል።



CamScanner

## ክፍል ሁለት

## ራእየ ዮሐንስ

### መግቢያ

**ራዕዩ ዘዮሐንስ ኤጺስ ቆጶስ ዘቁስጥንጥንያ መጠሮጶሊስ አመ ሀለም ይሰደድ**

ይህንን መጽሐፍ ስለሦስት ነገር ተናግሮታል። ደቀ መዛሙርቱ ያስተማራቸውን ገድፈውበት ለመገሠጽ፣ መዓርገ ካህናት ተሰጥቶት ወበዐውዱ ለውእቱ መንበር እስራ ወአርባዕቱ ብሎ ኋላ የሚያመጣው ነው። የጥጦስ፣ የሐሳዊ መሲሕ፣ የምጽአትን ነገር ለመናገር ነው። ኋላም ወእምዝ ርኢኩ ሰማየ ሐዲሰ ወምድረ ሐዳስ ብሎ የሚያመጣው የመንግሥተ ሰማያት ነገር ተገልጾለት ለመናገር ነው።

ጥንተ ነገሩ፡- ኖህ ሲም፣ ካም ፣ያፌት የተባሉ ልጆች ነበሩት ያፌት ይህያንን፣ ይህያን እስያን እንደ ወለደ እስያ ደግሞ ሰባቱ ዮናናውያንን ወልዷል። በቋንቋቸው በዮናኒ ዮናናውያን ተብለዋል። አይ አይደለም ቋንቋ በሰው ይጠራል እንጂ ሰው በቋንቋ አይጠራም ብሎ በአባታቸው በይህያን ዮናናውያን ተብለዋል። በሳዶቅ ሰዱቃውያን፣ በይሁዳ አይሁድ፣ በኤቦር ዕብራውያን እንደተባሉ አንድም በፀሐይ ያመልኩ ነበርና ዮናናውያን ተብለዋል። ጥንተ ዮን ፣አን እንዲል። ከሰባቱ ዮናናውያን በኩሩ ኤፌሶን ነው። ከኤፌሶን አርጤምስ የምትባል መልከመልካም ሴት ተወለደች። ቆርኔሌዎስ የሚባል ሥራኛ አግብታ ዜዎስ ሚባል ልጅ ወለደች። እነሱን በሕይወት እያሉ ከሞቱም በኋላ ሰይጣን በምትሐት እንደተነሡ እንዳረገ አድርጎ እያሳያቸው ሥዕላቸውን ስለው ምስላቸው ሠርተው የሚኖሩ ሆነዋል። ይህን ብቻ አይደለም ሰባቱን ከዋክብት ፣ፀሐይ ጨረቃን ሲያመልኩ ኖረዋል። ሰባቱ ከዋክብት ፡- እልሽምሽ፣ እልቀመር፣ መሪህ፣ መሽተሪህ፣ ዙሃል፣ አጣርድ ናቸው። በአጠቃላይ ዮናናውያን ከክርስቶስ ልደት አስቀድሞ ቅዱስ ዮሐንስ እስካስተማራቸው ድረስ በአምልኮ ጣኦት ይኖሩ ነበር ። ሐዋርያት ዓለምን በዕጣ ተካፍልው ለማስተማር በሄዱበት ጊዜ ለቅዱስ ዮሐንስ ምድረ ዕርዕ ደረሰችው ወደዚያ ለመሄድ ፈርቶ ሲያመነታ ቅስ ጴጥሮስ አጽናንቶት ሄዶ ወዲያው ሃይማኖታችሁን ልቀቁ አላላቸውም ። አስቀድሞ የሥነ ፍጥረትን ነገር ይነግራቸዋል። አርጤምስ ዜውስ ማለት የዕለተ ዓርብ ፍጥረቶች ናቸው። ዐሐይ ጨረቃ፣ ከዋክብትም የዕለተ

ረቡዕ ፍጥረቶች ናቸው ሁሉም ኃላፍያን ናቸው። ለማዩን ምድሩን፣ ባሕሩን የብሱን የፈጠረ አምላክ ብሎ አያይ፡ ጌታ ከፅንስ እስከ ዕርገት ያደረገውን ተአምራት የሠራውን ምግባር ትሩፋት ያስተማረውን ትምህርት (ወንጌል) ቢያስተምራቸው ከአምልኮተ ጣኦት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር፣ ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ ተመለሱ አመኑ ተጠመቁ ። ትምህርት ካልደረሰበት ለማዳረስ በሚሄድበት በሰባቱ ከዋክብት አንጻር ሰባቱ መንፈሳውያን ከዋክብት ኤጲስ ቆጶሳትን ሾሞላቸው ሄዷል። እንጾኪያን አስተምሮ ወደ ሶርያ ፣ ሶርያን አስተምሮ ወደ እንጾኪያ ሲመላለስ በባህረ ሉላግያ ማእበል ሞገድ ተነሥቶበት መርከቡ ተሰብሮበት አርባ ቀን ተንከራተተች ከማዕበሉ ጽናት የተነሣ ውቅያኖስ እየተከፈተ ይታየው ነበር በዚህ ሁኔታ ሳለ የእኔ ማስተማር ፈቃደ እግዚአብሔር ባይሆን ነው ብሎ አመለከተ። የበለጠ የጥጦስ፣ የሐሳዊ መሲሕ፣ የምጽአት ፣ የመንግሥተ ሰማያት ነገር ተገልጾለት ጽፏል። ከዚያም ለሰባቱ ከዋክብት መንፈሳውያን ኤጲስቆጶሳት የጻፈውን ልኮላቸዋል።

ይህ መጽሐፍ ራእየ ዮሐንስ የተባለው ስለመጨረሻው ዘመን በመንፈስ ሆኖ ያያቸውን ራዕያት ስለያዘ ነው። በግሪክ ቋንቋ አፖካሊፕስ ተብሎ ይጠራል። በእኛ አጠራር አቡቀለምሲስ ማለት ነው። ትርጉሙ የተጋረደ ነገር ተገልጦ መታቱን ያመለክታል። የክፋትን መጋረጃ አስወግዶ የጽድቅን ዓለም ስለሚያሳይ ነው።

የየሐንስ ራዕይ ከተጻፈበት ጊዜ ጀምሮ ለ276 ዘመን ያህል የነበረ ሲሆን በዲየቅልጥያኖስና በመክስምያኖስ የመከራ ዘመን የዮሐንስ ራዕይም ጠፍቶ ነበር። ሠለስቱ ምዕትም ለቅዱሳት መጻሕፍት ርዕስ ሲሰጡ ባያገኙትም ለራእየ ዮሐንስ ርእስ ሰጥተዋል። ይህ ከሆነ ከ150 ዘመን በኋላ ንጉሡ አርቃድዮስና ንግሥቲቱ አውዶክስያ በቁስጥንጥንያ በነገሡ ጊዜ የነበረው ኤጲስ ቆጶስ ዮሐንስ አፈወርቅ ንግሥት አውዶክስያ መፍቀሪተ ንዋይ ገፋዒተ ነዳይ ሆና እንዲት ድሀ መበለት በመበደሏ ምክንያት ስላወገዛት በደሴተ አጥራክያ አጋዘችው በዚያ ጊዜ እንደ ልማዱ መጻሕፍትን ሲመለከት የዮሐንስ ራዕይን አግኝቶታል። አንድም ሌሎቹን መጻሕፍት ሲያገኝ የሐንስ ራዕይን አላገኘውም ነበር በጸሎት ንባቡ ከነትርጓሜው ተገልጾለት ጽፏል። በዚህም ሐዲስ ዳንኤል ተብሏል፣ ዳንኤል የናቡከደነጾር ሕልም ከነትርጓሜው ተገልጾለት እንደናገረ የኋላ ሰዎች ለዮሐንስ አፈወርቅ አርእስት ሰጥተዋል፤ዮሐንስ አፈወርቅ ለዮሐንስ አርእስት ሰጥቷል። ጳሊስ ሊቅ መጥራ መዲና ማለት ነው። የመዲናይቱ የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ በስደት ጊዜ ያገኘው ዮሐንስ ወንጌላዊ ያየው ራዕይ የህ ነው።



CamScanner

**ጸሐፊው**

የዮሐንስ ራዕይ ጸሐፊ 4ኛው ወንጌል የጻፈው ዮሐንስ ወንጌላዊ ነው፡፡ ለዚህም ሁለት ዓይነት መረጃዎች አሉ፤ እነሱም ፡-

1. ዮሐንስ የመጽሐፉ ባለቤት ሆኖ በራሱ በዮሐንስ ራዕይ ውስጥ አራት ጊዜ ያህል ጠቅሷል፡፡ /1፡1-2፤1፡5፤1፡9፤22፡8
2. ዮሐንስ ወንጌሉ ውስጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የእግዚአብሔር በግ እና ይግዚአብሔር ቃል ብሎ ጠርቶታል፡፡ ዮሐ. (1፡1፤14. 1፡19) በራዕየ ዮሐንስም ኢየሱስ ክርስቶስን የእግዚአብሔር ቃል ብሎ ጠርቶታል፡፡ (5፡6-12፡1017፤14፡1፤19፡13) ወንጌሉና ራዕዩ በዚህ አገላለጽ መመሳሰላቸው ራእየ ዮሐንስን ያጻፈው 4ኛውን ወንጌል ወንጌል የጻፈው ዮሐንስ ወንጌላዊ መሆኑን ያስረዳል፡፡

**የተጻፈበት ቦታና ዘመን**

ራዕየ ዮሐንስ የተጻፈበት ቦታ በደሴተ ፍጥሞ ነው፡፡ ራዕዩን ያየውም በዚህ ቦታ እንደነበር በግልጽ ተነግሯል፡፡ (1፡9) ፍጥሞ ከኤፌሶን በስተ ደቡብ ምዕራብ በኤጅያን ባሕር ውስጥ የምትገኝ ትንሽ ደሴት ነች፡፡ ይህቺ ቦታ በሮማ መንግሥት ላይ ያመፁ ሰዎች የሚታሠሩባት ደረቅና ድንጋያማ የሆነች ምድረ በዳ ቦታ ናት፡፡ ዮሐንስም ከ81-96 ዓ.ም በነገሠው በድምጥያኖስ (በዶሚታያን) ዘመን ንጉሱ እንዲሰግድለት በኤፌሶን ያቆመውን ምስል በመቃወሙ በዚህች ደሴት እንደታሠረ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል፡፡ ስለዚህ ራዕዩ የተጻፈበት ዘመን 96 ዓ.ም ገደማ እንደሆነ ሊቃውንት ያስረዳሉ፡፡

**ሰባት ቁጥር በራዕየ ዮሐንስ**

በዮሐንስ ራዕይ ተደጋግመው ነገሮች አንዱ ሰባት ቁጥር ነው፡፡

- ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ራዕ.1፡4 እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በ7ቱ መቅረዞች ተመስለዋል፡፡
- ሰባቱ መንፈሶች አንዳንድ ሊቃውንት ሰባቱ ሊቃነ መላእክት ናቸው ሲሉ ሌሎች ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ፍጹም የሆነህብት/ ሥራ/ የሚያመለክት ነው ብለው ተርጉመውታል፡፡
- ሰባቱ የእሳት መብራቶች የሰባቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ምሳሌዎች ናቸው፡፡ (ራዕ 5፡1)

- ሰባቱ ቀንዶች (ራዕ.5፡6) ዮሐንስ በዙፋኑ ላይ ያየው በግ ሰባት ቀንዶች ነበሩት፡፡ ቀንድ የኃይል ሥልጣን ምሳሌ ነው፡፡
- ሰባት ዓይኖች (5፡6)ኢየሱስ ክርስቶስ ማዕምረ ኩሉ ማእምረ ኀቡኣት መሆኑን ያመለክታል፡፡
- ሰባት ሺ ሰማዕታት (11፡13) በሐሳዊ መሲሕ የሚገደሉትን ሰማዕታት በፍጹም ቁጥሮ ነው፡፡
- ሰባት ራሶች (12፡3) አውሬው ሰባት ራሶች ሉት መሆኑ ከዚያ በፊት ታይቶ የማያውቅ ፍጹም አስቃቂ መከራ በቤተ ክርስቲያን መምጣቱን መናገር ነው፡፡
- ሰባት ተራሮች (ራዕ.17፡9) አመንዝራዋ ባቢሎን የተቀመጠችባቸው ተራሮች ሰባት ናቸው፡፡

## የዮሐንስ ራዕይ አጠቃላይ ይዘት

የዮሐንስ ራዕይ አተቃላይ ይዘት ትንቢት ነው፡፡ ነገር ግን በትንቢት ውስጥ ለሃማኖትና ለምግባር እንዲሁም ለሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ የሆኑ ትምህርቶች ይገኙበታል፡፡ የያዛቸው ትንቢቶች በዮሐንስ ዘመን ስላለውና ወደፊት ስለሚሆነው ነገር የሚገልጡ ናቸው፡ ትንቢቶቹም ለዮሐንስ የተገለጡት በራዕይ ነው፤ ራዕዩም በምሳሌያዊ ነገሮች የታየ ራዕይ ነው፡፡



CamScanner

## ምዕራፍ አንድ

(1). ራዕዩ ለዮሐንስ ዘከመ ርእዮ ለእግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ

-ኢየሱስ ክርስቶስን እንዳየው መጠን ያየው ራዕይ አንድም ዮሐንስ ወንጌላዊ ኢየሱስ ክርስቶስን እንዳየው ዮሐንስ አፈወርቅ ያየው ራዕይ ይህ ነው፡፡

-ዮሐንስ ለአግብርቲሁ ለወደዱት (ለደቀመዛሙርቱ) ያስተምራቸው ዘንድ እግዚአብሔር የገለጸለት ራዕይ ይህ ነው፡፡

(2). ኢየሱስ ክርስቶስ የመሰከረውን የጻፈ እምቅድመ ይትወለድ አብርሃም ሀሎኩ አነ (አብርሃም ሳይፈጠር ነበርኩ) ብሏል ብሎ የኢየሱስ ክርስቶስ የህልውናውን፣ የጌትነቱን የቅድሞናውን ነገር የመሰከረ ቀዳሚሁ ቃል ብሎ፡፡ አንድም የወንጌልን ነገር የመሰከረ የኢየሱስ ክርስቶስ የምስክሩንም ነገር ጻፈ ዮሐንስ መጥምቅ የመሰከረውን (ማለት ነው) ዮሐንስ ሰማዕቱ ብሎ በእንቲአሁ ከልሐ ወይቤ ነዋ በግዑ ብሎ፡፡ ስላየውም ነገር የመሰከረ ምን አይቷል ቢሉ ከጎኑ ትኩስ ደም ጥሩ ውሃ ሲፈስ አይቷል፡፡

(3). ወብፁዕ ውእቱ ዘያነብቦ የሚደግመው ሰው ንዑድ ክቡር ነው፤ ድጋሙን የሚሰማው፣ ምስጢሩን የሚያስተውለው ብፁዕ ነው፡፡ ከጠፋ የተገኘበት ዋጋ የሚያሰጥበት ዘመኑ ቅርብ ነውና ከጠፋ የተገኘበት 150 ዕሜት የሚያሰጥበት እንደ ዐቃቤ ሰዓት ዐበሞ

(4). ዘጸሐፈ ዘጸሓፍኩ ሲል ነው በእስያ በሰባቱ አህጉር ላሉ ምእመናን የጻፋኩት ራዕይ ይህ ነው

(7). ናሁ ይመጽእ በደመና ሰማይ በበጎዎች መምህራን አድሮ ክፉዎቹን ለመገሰፍ ለመንቀፍ ይመጣል በኤልያስ አድሮ አክአብን በዮሐንስ አድሮ ሄሮድስን እንደዘለፈ ደመና አላቸው በጎዎችን መምህራን ደመና ከውቅያኖስ ገዘናም ቋጥሮ ወጥቶ እየዞረ እያዘነመ ለብዙ አገዘርዕት አትክልት ይጠቅማል እነሱም ዞረው አስተምረው ያልተመሰለውን መስለው የተመሰለውን ተርጉመው ብዙ ምእመናንን ይጠቅማሉና፡፡ አንድም በባሕርይ ክብሩ ይመስላል የምጽአት፣ የዕርገትና የታቦር ደመና የባሕርይ ክብሩ ነውና፡፡ አንድም በሥጋ ማርያም በክበበ ትስብእት ይመጣል፡፡ ፍጥረት ሁሉ በርእይ ታየዋለች ጎኑን የወጉትም ያዩታል፡፡



CamScanner

(8). እነ ውእቱ አልፋ ወኦ አልፋ አ እኔ ነኝ አ አብ፣ ል ወልድ፣ ፍ መንፈስ ቅዱስ ኦ አንድነት ፤ አንድነት ሦስትነት ገንዘቤ የሚሆን፡፡ አንድም ቀዳማዊ ደኃራዊ የምሆን እኔ ነኝ፡፡

(9). በልጅነት ወንድማችሁ የምሆን ታግሣችሁ በምትቀበሉት መከራ ተባባሪያችሁ የምሆን እኔ ዮሐንስ ፍጥሞ በምትባል ደሴት ሳለሁ ፍጥሞ ማለት መካነ ኀህል መካነ ራዕይ ማለት ነው፡፡

(10). እሑድ በሚባል ቀን መንፈስ ቅዱስ አደረብኝ ማለት ሥራ አሠራኝ ሲል ነው፡፡ አንድም በዕለት እሑዱ ከዕለታት በአንድ ቀን መንፈስ ቅዱስ አደረብኝ፡፡ ከወደ ኋላዬ እንደ ነጋሪት ያለ ቃል ሰማሁ ቀርን አለ፡፡ ነጋሪት ፈጥኖ ፈጥኖ ይመታል፤ ራዕዩ ፈጥኖ ፈጥኖ ይሰማዋልና አንድም ነጋሪት የራቀውን ያቀርባል የቀረበውን ያርቃል፤ ራዕዩም የቀረበውን አርቆ የራቀውን አቅርቦ ያሳየዋልና፡፡ አንድም ነጋሪት ከሩቅ ይሰማል ራዕዩም ጽንፍ እስከ ጽንፍ ደርሷልና፡፡

(11). የምታየውን የምትሰማውን በዚህ መጽሐፍ ጻፍ አለኝ ያን ጊዜ ተጽፎ አይደለም በኋላ ስሙ መጽሐፍ ብሎታል ምን አይቷል ምን ሰምቷል ቢሉ ከወደፊቱ ብርሃን አይቷል ከወደኋላው ቃል ሰምቷል ቢሉ ፡ ጽፈሕ በእስያ ባሉ ሰባቱ አህጉር ላሉ ምእመናን ሰደድ (ላክ) አለኝ፡፡

- ✓ ኤፌሶን
- ✓ ሴሜርኔስ
- ✓ ትያጥሮን
- ✓ ሰርዴስ
- ✓ ፊልድልፍያ
- ✓ ሎዶቅያ

እስያ ከታናሽ እስያ አውራጃዎች አንዷ ስትሆን እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ሰባቱ ከተሞች ደግሞ በውስጧ ይገኙ ነበር፡፡ ዮሐንስ ከእነዚህ ከተሞች ውስጥ በኤፌሶን ለረጅም ጊዜ ተቀምጦ ሳለ ሰባቱንም አብያተ ክርስቲያናት ያውቃቸው እንደነበር ከጻፈላቸው መልእክታት ይዘት እንገነዘባለን፡፡ ዮሐንስ የሚያየውን በመጽሐፍ ጽፎ ለእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት እንዲልክ ታዝዞ ነበር፡፡ /1፡10-11/ ስለዚህ በመግቢያው ላይ ዮሐንስ በእስያ ላሉት ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ይላል /1፡5

**1. የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን፡-** ኤፌሶን ማለት ‹‹መፈለግ›› ማለት ነው፡፡ ተደጋግሞ እንደተገለጠው ኤፌሶን የእስያ ዋና ከተማ ስትሆን የምትገኘውም በኤጅያን ባሕር ዳር ነበር፡፡



CamScanner

ቅዱስ ጳውሎስ በዚህች ከተማ በመጀመሪያ አቂላና ጵርስቅላን አስተምሮ በእርሱ ወንጌል እንዲሰበክ ካደረገ በኋላ ቀጥሎም ራሱ መጥቶ ለሦስት ዓመት ያህል እንደሰበከ የሐዋርያት ሥራ ያስረዳል፡፡ /18፡18-28፣ 20፡31 የሐዋርያት ሥራ 19፡10 በዚህ ጊዜ ውስጥ በእስያ ሁሉ ወንጌል እንደተዳረሰ ስለሚገልጽ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የተመሠረቱት በዚያ ጊዜ እንደሆነ ሊቃውንት ይናገራሉ፡፡ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን በኤፌሶን ሹሞት ነበር 1ጢሞ.1፡4፡፡ ዮሐንስም እስከ ሕይወቱ መጨረሻ አካባቢ ወንጌልን የሰበከው በኤፌሶን እንደነበር የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል፡፡

2. **የሰሜርኔስ ቤተ ክርስቲያን፡-** ሰምርኔስ ማለት ‹‹በርቤ›› ማለት ነው፡፡ ከኤፌሶን በስተሰሜን 65 ኪ..ሜ ገደማ ርቃ የምትገኝ ከተማ ናት፡፡ በባሕሩ ዳር የምትገኝ ወደብም ነበረች፡፡ የሮም መንግሥት ታማኝ ደጋፊ ነበረች፡፡ በጢባርዮስ ቄሣር ዘመን በከፍተኛ የመሬት መንቀጥቀጥ ይከሰትባት ነበር፡፡ ነገር ግን እንደገና ጴንሱ በተባለው ተራራ ላይ ተሠርታለች፡፡

3. **የጴርጋሞን ቤተክርስቲያን፡-** ጴርጋሞን ማለት ‹‹ጋብቻ›› ማለት ነው፡፡ ይህቺ ከተማ ከሰምርኔስ በስተሰሜን 6 ኪ..ሜ ርቃ የምትገኝ ከተማ ናት፡፡ ወደ 14.000 የሚደርስ ሕዝብ ይኖርባት ነበር፡፡ በውስጥዋ ወደ 200.000 ያህል የሚሆኑ መጻሕፍትን የያዘ ትልቅ ቤተ መጻሕፍት እንደነበረባት ይነገራል፡፡ በከተማይቱ አሕዛብን ያመልኩ የነበረው ንጉሡን ነበር፡፡ በከተማይቱ መካከል ሥራው አስደናቂ የሆነ ትልቅ ቤተ ጣዖትና መሠዊያ ነበር፡፡ የጣዖታቸው ምልክትም የእባብ ምስል ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ጴርጋሞን በዚያ ዘመን የእስያ ዋና ከተማ የነበረች ስትሆን ዛሬ ግን ከተማይቱ በነበረችበት ቦታ ምንም ነገር የለም፡፡

4. **የትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን፡-** ትያጥሮን ማለት የዘወትር መሥዋዕት ማለት ነው፡፡ በጴርጋሞን በደቡባዊ ምሥራቅ በኩል 100 ኪ..ሜ ገደማ ርቃ የምትገኝ እና ብዙ የንግድ ሥራ የተስፋፋባት ከተማ ነበረች፡፡ በተለይም በሐር ንግድ ትታወቃለች፡፡ በፊልጵስዮስ በጳውሎስ ስብከት ያመነች ልድያ የተባለችው የትያጥሮን ሴት እንኳ ሐር ሻጭ እንደነበረች ተገልጧል የሐዋ ሥራ.16፡14 ከዚህም ሌላ ልብስ በማቅለም ሥራ የታወቀች ከተማ ነበረች በተለይም በቀይና በሐምራዊ ቀለማት ልብሶችን ታቀልም ነበር፡፡ በአሁን ጊዜ በዚያ ቦታ ያለችው ከተማ አኪሳር የምትባል ትልቅ ከተማ ናት፡፡

5. **የሰርዴስ ቤተክርስቲያን፡-** ሰርዴስ ማለት ‹‹ማምለጥ››ማለት ነው፡፡ ይህች ከተማ ከትያጥሮ በደቡብ ምሥራቅ 50 ኪ..ሜ ገደማ ርቃ ትገኛለች፡፡ በጣም ዝነኛና ሀብታም ከተማ ነበረች

የከተማዋ ትጥር የተገነባው በከፍተኛ ተራራዎች ላይ ስለነበር በዚህ ምክንያት የሰርዴስ ሰዎች ማንም አይደፍረንም በማለት በከተማዋ መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ ይመኩ ነበር። ይሁን እንጂ በአሁኑ ጊዜ በዚያ ሥፍራ ከፍርስራሽ በቀር ምንም ነገር የለም።

6. **የፊልድልፍያ ቤተ ክርስቲያን፡-** ፊልድልፍያ ማለት ‹‹የወንድማማች ፍቅር ማለት ነው። የልድያ ሁለተኛይቱ ከተማ ነበረች። ከተማይቱን የቆረቆራት ንጉሥ ለሚወደው ወንድሙ መታሰቢያ እንድትሆን ስላደረጋት፤ ፊልድፍያ ብሎ ሊሰይማት ችሏል። ከሰርዴስ በስተደቡብ ምሥራቅ 40 ኪ.ሜ ርቃ የምትገኝ ከተማ ናት። ፊልድፍያ የተመሠረተችው በተራራዎች መካከል ባለ ሸለቆ ውስጥ ነበር። እንደገና የተሠራች ብትሆንም በ17 ዓ.ም በመሬት መንቀጥቀጥ ፈርሳ ነበር። በአሁኑ ጊዜ ይህቺ ከተማ አላሳሕር ተብላ ትጠራለች።

7. **የሎዶቅያ ቤተክርስቲያን፡-** ሎዶቅያ ማለት የሰዎች አገዛዝ ማለት ነው። የፍርግያ ክፍለ ሀገር ዋና ከተማ ነበረች። ከኤፌሶን በስተምሥራቅ 60 ኪ.ሜ. ያህል ርቃ ትገኝ ነበር። ሰፊ ቦታ ይዛ የነበረች ከተማ ናት። በውስጥዋ ከ20 እስከ 30 ሺሕ ተመልካቶችን የሚይዝ የቲያትር ስፍራ እንደነበራት የታሪክ አዋቂዎች ይናገራሉ። ነገር ግን በአንድ ወቅት በመሬት መንቀጥቀጥ ፈርሳ እንደገና ሠርተዋት ነበር። በከተማይቱ ውስጥ በድንጋይ ቧንቧ የሚፈስ ለብ ያለ ውኃ ነበር። ከዚህም ሌላ የሱፍ ልብሶች የሚመረትበት የዐይን ኩል የሚዘጋጅባት ሀብታም ከተማ ነበረች። በአሁኑ ጊዜ የጥንቷ ከተማ ከፍርስራሽ በቀር በቦታዋ የሚታይ ነገር የለም። ነገር ግን ዶሊዝሊ የምትባል ከተማ በቦታው አጠገብ ትገኛለች። የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ጳውሎስ ያውቃት ነበር ቆላ.2፡1። በሎዶቅያ ውስጥ ንምፋን በተባለ ሰው ቤት ቤተ ክርስቲያን ነበረች። ቂላ.4፡15። የቆላስይስ መልእክት በሎዶቅያ ቤተክርስቲያንም እንድትነበብ ጳውሎስ አገዟል። ሎዶቅያ 13 ማይል ወይም 20 ኪ.ሜ ወደ ምዕራብ ርቃ ትገኛለች። ጳውሎስ በእነዚህ ሁለት የተቀራረቡ ከተሞች ላሉ አብያተ ክርስቲያናት ትልቅ መጋደል ነበረው ቆላ. 2፡1። ከአንደኛው የሮም እስራቱ በኋላም በሎዶቅያ ተገኝቶ አስተምሮ እንደነበር ታሪኮች ይናገራሉ።

አንድም ከነገረ ሥጋዊ አንጻር ሲተረጎም ኤፌሶን ማለት አፈ ሳን ማለት ነው፤ አፈሳንም ማለት ቃለ አብ ማለት ነው። በእሱ ላመኑ። ሴሜርኔስ ማለት ዘሠምረ ይኩን ሰብአ ማለት ነው በእሱ ላመኑ ጴርጋሞን ማለት ዘለብሰ ሥጋማለት ነው። (ጥቅ) ብእሲ ዘይለብስ ጠብዶነ እንዲል። በእሱ ላመኑ ፊልድልፍልያ መፍቀ ማለት ነው በእሱ ላመኑ ትያጥሮን ማለት ቅውም ማለት ነውበእሱ አምነው ላሉ። ሰርዴስ ማለት ዘትስልስት ወዘተዋሕዶ ማለት ነው። በእሱ አምነው ላሉ። ሎዶቅያ ማለት ቃል ቀዳማዊ ማለት ነው። በእሱ አምነው ላሉ። ጽፈሕ ስደድ አለኝ።



CamScanner

(12) ሰባት የወርቅ ፋና አየሁ ወርቁና ፋናው እንደ ሰምና ፈትል ተጣምቶ ሲነድ ያየዋል። ፈትሉ የሰውነታቸው፣ ወርቁ የንጽሕናቸው፣እሳቱ የመከራቸው ብርሃኑ የጸጋቸው ምሳሌ ነው ተዋሕዷቸዋል።

(13) በሰባቱም የወርቅ ፋና መካከል ወልደ እጓለ እመሕያው ተቀምጧል አለ ተዋሕዷል። ወየለብስ ልብሰ ጰዴር እንደ ንጉሠ ነገሥትነቱ አርዕድ አንቀጥቅጥ የሚባል ልብሰ መንግሥት ለብሷል። የወረወቅ አፋ ታጥቋል። ትእምርተ ኃይል ነው አንድም እንደ ሊቀ ካህንነቱ ሞሉጣ ለብሷል። የወርቅ ዝናር ታጥቋል ማለት ትምርተ ተልዕኮ ነው። አንድም ሥጋን ተዋሕዷል። ጽንዐ ተዋሕዶንገንዘብ አድርጓል።(14) ራስ ቅሉ ነጭ ነው ጽርየተ ባሕርዩን መናገር ነው። ጠጉሩም እንደ ነጭ ግምጃ ነው እንደ ግምጃ ነጭ ነው። ብሉየ መዋዕልነቱን መናገር (15) ዐይኖቹ እንደ ነደ እሳት ነው እግሮቹም በእሳት እንዳፈሉት እንደ ደጋ ብረት ናቸው። ትእምርተ በቀል ትእምርተ መዓት ነው። አንድም አእይንቲሁ ነቢያት ናቸው አእይንት አላቸው ምስጢር ያያሉና። እገሪሁ ሐዋርያት ናቸው ሑሩ ወመሐሩ ብሏቸዋልና። አንድም አእይንቲሁ ቀሳውስት ናቸው ምስጢር ያያሉና እገሪሁ ዲያቆናት ናቸው በተልእኮ ይኖራሉና። (16) ፊቱ በቀትር ጊዜ በግድ እንደሚታይ ፀሐይ ነው። በክበቡ አብ፣ በብርሃኑ ወልድ፣ በሙቀቱ መንፈስ ቅዱስ (20) በቀኝ እጁ ተይዘው ያየሃቸው የሰባቱ ከዋክብት፣የሰባቱ የወርቅ መቅረዝ/ፋና ትርጓሜያቸው ይህ ነው።ሰባቱ ከዋክብት በሰባቱ አህጉር ባሉ ምእመናን ላይ የተሾሙ ሰባቱ መንፈሳውያን ከዋክብት ኤጲስ ቆጶሳት ናቸው። ሰባቱም የወርቅ መቅረዝ በሰባቱ አህጉር ያሉ ሰባቱ ምእመናን ናቸው።



CamScanner

ምዕራፍ ሁለት

ወፈነ ለአብያተ ክርስቲያናት ሰብአቱ (1፡11) ብሎ ነበርና እነዚህን ይዘረዝራል

መልአከ ኤፌሶን ስሙ ዮሐንስ ሁለተኛ ስሙ ደማትሪ ይባላል። ለሱ ጻፍለት አለኝ። አኃዜ ኩሉ ሁሉን ፈጥሮ የሚገዛ እሱ እንዲህ አለኝ ብለህ ። ሰባቱን ከዋክብተት በእጁ ያጸና አንድም ሰባቱን መንፈሳውያን ኤጲስ ቆጶሳትን በሥልጣኑ ያጸና። በሰባቱ የወርቅ መቅረዘ/ፋና መካከል የሚሄድ ከዚያ ይነብር አለ ከዚህ የሐውር አለ እንደምን ነው ቢሉ ኃጢአት ሲሠሩ ይለያቸዋልና የሐውር አለ ጽድቅ ሲሠሩ ያድርባቸዋልና ይነብር አለ።

(2) ሥራህን ድካምህን፣ መከራውን መታገሥህን አውቃለሁ። ሳይሆኑ ሐዋርያት ነን የሚሉትንም መታገሥ፣ ገዝም ማለት እንዳቻልህ አውቃሁ።

(3) በስሜ ስላመንክ ስሜን ስላስተማርክ በስሜ ስለተጠራህ መከራውን ታግሠህ ተቀብለሃል፣ መካራውን አልሰለችህም።

(4) ነገር ግን የምነቅፍብህ አለኝ በዚህ አልነቅፍህም በሌላው እነቅፍሃለሁ ማለቱ ነው። የቀደመ ሥራህን (ፍቅርህን) ትተሃልና ሥራው ምንድን ነው ቢሉ አልታወቀም። አንድም ታውቋል። ምትዋት ነበረ የተወበት ምክንያት አልታወቀም።

(5) አስተውል ምጽዋቱን ለምን ተውክ ምጽዋት አያጸድቅም አሉህ ገበሬ ከእርበተ ፀሐይ በፊት ሥራውን ይፈታልን እንደዚህስ ከሞት አስቀድመህ ምጽዋቱን ለምን ተውክ ማለት ነው። ተው ተመለስ ያለዚያ ግን (ባትመለስ) እንደ ቀድሞው ሥራህን ባትሠራ በመዓት መጥቼ ሕዝቡን ከኤፌሶን አጠፋቸዋለሁ። ሕዝቡ ቢጠፋ እሱ ምን ይጎዳልቢሉ ሕዝቡ ከጠፋ በማን ላይ ይሾማል። አንድም ሹመትህን ከማዕርጌ አዋርዳታለሁ። አንድም ነፍስህን ከሥጋህ እለያታለሁ።

(6) ይህን ግን ይዞሃል። የኒቆላውያንን ግብር እንደምጠላ አንተም ትጠላለህና። ኒቆላውያን ግብረ ሰዶም የሚሠሩ ናቸው። ጥምቀት በሠላሳ ዓመት ግዝረት ባርባ ዓመት የሚሉ የኒቆላዎስ ዘሀገረ አንጾኪያ ደቀ መዛሙርት ናቸው። ይህስ ቢሆን ሐዋርያት በዘመኑ ነበሩና ብዙ ድረሰት በደረሱ ብዙ ተግሣጽ በጻፉ ነበር ብሎ ሌላ ስመ አበር ግብረ አበር

(7) ዘዐ ዕዝን ሰሚዐ ለይስማዕ የኒቆላውያንን ግብር ድል የነሣ እንዳይጎዳ ድል ያልነሣ እንዲጎዳ ዕዝነ ልቡና ያለው ያስተውል እንድም ፍቅረ ንዋን በፍቅረ ቢጽ ደል የነሣ እንዳይጎዳ ድል የነሣ እንዲጎዳ እዝነ ልቡና ያለው ያስተውል።

ላለቃው ይህን ተናገረ ለሕዝቡ ምን ተናገረ ትለኝ እንደሆነ ላለቃው የተናገረው ለሕዝቡም ነው። እንድም ላለቃው የተናገረ ለሕዝቡም የኒቆላውያንን ግብር ድል የነሣ እንድም ፍቅረ ንዋይን በፍቅረ ቢጽ ድል ለነሣ በፊጣሪየ በገነት ካለ ዕፀ ሕይወት የበላ ዘንድ እሰጠዋለሁ አለ ልጅነትን እሰተዋለሁ እንድም ሥጋወደሙን እሰጠዋለሁ። እንድም በፍቅሩ ተሠውራ ለች ፍቅሩን እሰጠዋለሁ።

(8) መልአከ ሴሜርኔስ (ሰምርኔስ) ስሙ ሄሬኔዎስ ሁለተኛ ስሙ ኢያሳ ነው ለእሱ ጻፍለት አለኝ። ቀዳማዊ ደኃራዊ የሚሆን ሞቶ የተነሣ እሱ እንዲህ አለ ብለህ ጻፍለት አለኝ ብለህ ጻፍለት። (9) ንዴትህን አውቃለሁ፣ ከብዕለ ዓለም መቸገርህን አውቃለሁ ነገር ግን ባለ ጸጋ ነህ ምእመናን ሳይሆኑ ነን የሚሉትን በመንቀፍ ባለጸጋ ነህ እንድም ሕምመከ መከራህን ወኃጣይዕከ ከብእለ ኃጢአት መቸገርህን አውቃለሁ ባለጸጋ ነህ ሳይሆኑ ምእመናን ነን የሚሉትን በመንቀፍ እንድም መንቀፍህን አውቃለሁ ፡ የሰይጣን አሻክርት ናቸው እንጂ

(10) ነገር ግን መከራ መቀበልን አትፍራ እነሆ ሰይጣን ከእናንተ ወገን እንድትጋዙ ያደርጋልና። መከራ የለብንም እንዳል መከራ መቀበልን አትፍራ አለ በእኔ ብቻ ነው እንዳል ሰይጣን ከእናንተ ወገን እንድትጋዙ ያደርጋል አለ የሺ ሞት ሰርግ ብሎ እንዳይዘለል (እንዳይዘናጋ) ተሐሙ ይላል አስር ቀን መከራ ትቀበል ዘንድ አለህና ይህ ሰው አስር ቀን ታሥሮ ሰንብቶ በሰማዕትነት ሙቷል። እስከ መሞት ደርሰህ ጽና። መንግሥተ ሰማያትን አወርሳለሁና መንግሥተ ሰማያትን አክሊል አላት የብዕለ ሥጋ ፍጻሜው ዘውድ እንደሆነ ብለ ፍጻሜው መንግስተ ሰማያት ናትና። (11) ክህደትን በሃይማኖት ፍርሐትን በጥብዓት ድል የነሣ እንዳይጎዳ ድል ያልነሣ እንዲጎዳ እዝነ ልቡና ያለው ያስተውል።

(12) መልአከ ጴርጋሞን ስሙ ጋይስ ሁለተኛ ስሙ ጠብዶን ለሱ ጻፍለት አለኝ። ሁለት ልሳን ሰይፍ ያለው እሱ እንዲህ አለ ንዑና ሁሩ በቃሉ የሚናገር እሱ እደ ሥጋህን ለጸሎት እደ ቃልህን ለትምህርት ያኖርክባቸው ሰዎች የሰይታን ማደሪያ እንደሆኑ አውቃለሁ። አምልኮቴን አጽንተህ ይዘሃል። ሃይማኖቴን አለወጥክም ሰይጣን ያደረባቸው ሰዎች ወዳጁ ምእመንን በገደሉበት ወራት ሰይጣንም ተበረታቶበት በነበረ ወራት አልካድክም የዚህ ሰው ስሙ ስምኦን፣



CamScanner

ሮዳሂ፣ ምናሴ፣ መስም እንቴጳስ ይባላል ። (14) ነገር ግን የምነቅፍብህ አለኝ የባላቅ የመምህሩ የበለዓምን ግብር የያዙ አሉና። በለዓም የቀደመ በለዓም ነው። እንድም ሌላ ስመ አበር ግብረ አበር ነው። እንድም ቤተ አይሁድ ናቸው በለአም ለጣኦት ስገዱ መሠዋዕተ ጣኦቱን ብሉ ይል እንደነበር ቤተ አይሁድም ሕገ ኦሪትን ብሉ ይላሉ። ለጣኦት የተሠዋውን መሥዋእት ይበሉ ዘንድ ለጣኦቱ ይሰግዱ ዘንድ ለእስራኤል ልጆች ክህደትን የሚያስተምሩ አሉና። ዘኁ 31፡16፣ ይሁዳ 11.

**ምዕራፍ ሁለት**

**ጌታችን በቃና ያደረገው የመጀመሪያ ተአምር**

**ወአመ ሣልስት ዕለት ከብካብ ኮነ በቃና ዘገሊላ**

የገሊላ ክፍል በምትሆን በቃና በሦስተኛው ቀን ሠርግ ተደረገ፡፡ ጌታ ማክሰኞ ተጠምቆ ዕለቱን ሄደ፡፡ አርባው ቀን ቅዳሜ ይፈጸማል፡፡ እሑድ ገብቶ ያድራል፡፡ ዐርባውን ቀን እንደ አንድ አድርጎ እሑድን ለዐርባው ቀን ሳኒታ አለው፡፡ በማቴዎስ ሃያ አምስቱን ዘመን እንደ አንድ አድርጎ ወበውእቱ መዋዕል እንዳለ፡፡

እመቤታችን ከሠርግ ቤት ነበረች ቤተ ዘመድ ናትና አንድም ደግ ናትና ተጠርታ ገታን ጠሩት፡፡ እናት ጠርቶ ልጅን መተው ሥርዓት አይደለምና፡፡ ደቀ መዛሙርቱንም ጠሯቸው መምህር ጠርቶ ደቀ መዝሙር መተው ሥርዓት አይደለምና፡፡ ጠጁ ባለቀባቸው ጊዜ ወይንኬ አልቦሙ እመቤታችን ጠጅ እኮ አልቆባቸዋል አለችው፡፡ ይህ የእመቤታችንን አማላጅነት ያመለክታል፡፡ እሱ የማያውቅ ሆኖ አይደለም ኩሉ ዘይቤለክሙ ግበሩ ለማለት ነው እንጂ፡፡ አንቺ ሴት ካንቺ ጋር ምን አለኝ ሴት ማለት ሥጋሽ ከሥጋዬ፣ አጥንትሽ ከአጥንቴ ማለት ነው፡፡(ዘፍ.2፡3) አንድም ሴት ማለት ምትክ ማት ነው፡(ዘፍ.2፡--) ጌታችን እመቤታችንን በዮሐንስ ወንጌል ብቻ ሁለት ቦታ አንቺ ሴት ብሏታል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም ወአመ በጽሐ እግዚአብሔር ፈነወ ወልዶ ወተወልደ እምብእሲት ቀጠሮው በደረሰ ጊዜ ከሴት ተወለደ፡፡(ገላ 4፡4) በማለት ገልጧታል፡፡ እመቤታችን ከሐናና ከኢያቄም የተወለደች ፣ከሰው የተገኘች እንጂ ኃይል አርያማዊት አለመሆኗን መረዳት ወሳኝ በመሆኑ ነው፡፡ ካንቺ ጋር ምን አለኝ ማለት እመቤታችችን ለመንቀፍ ሳይሆን አድርግ ያልሽንን ላለማድረግ ካንቺ ጋር ምን ጠብ አለኝ ማለት ነው፡፡ አንድም በአምላክነቱ አገብሮ፣ ተአዝዞ/ መገደድ፣ መታዘዝ/ የሌለበት መሆኑን ለማጠየቅ ነው፡፡ ጊዜየ አልደረሰም፡፡ ሥረውን የሚሠራበት ጊዜ አለውና አንድም ጠጁ ፈጽሞ አላለቀም ነበርና ያለውንም አበርክቶት ቢሆን ተአምራቱ ባለተደነቀም ነበር፡፡ አንድም ይሁዳ ወጥቶ ነበርና ይሁዳ ሳይኖር ተአምራቱቱን አድርጎት ቢሆን ከሞቱ የገባሁት ከተአምራቱ ስለለየኝ ነው ብሎ ምክንያት በሆነው ነበር፡፡

እመቤታችን የዘዛችሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸው፡፡ ውሃውን ወይን እንደሚያደርገው ታውቅ ነበርና፡፡ ከዚያ 6 የደንጊያ ጋኖች ነበሩ፡፡ ሁለት፣ ሁለት ሦስት፣ ሦስት ማድጋ ይይዛሉ፡፡ 3ቱ ሁለት ሁለ፤ት (6) 3ቱ ሦስት ሦስት(9) ይይዛሉ 15 ይሆናል፡፡ አንድም ስድስቱ በታናናሽ



CamScanner

ሦስት፣ ሦስት ይይዛሉ (3*6) 18 ይሆናል። አንድም ስድስቱ በታላላቅ ሁለት፣ ሁለት ይይዛሉ 12 ይሆናል።

ቀድታችሁ ወስዳችሁ ለአሳዳሪው ስጡት አላቸው። ተአምራትስ ያደርጋል ነገር ግን አስተዳደር አያውቅም እንዳይሉት አንድም ሁሉ ጠጥቶ ሰክሯል ጣዕም አያውቅም እርሱ ግን ያውቃል ብሎ አሳዳሪው ቀምሶ አደነቀ። ካመጡበት ግን አላወቀም እነሱ ግን ጠጅ የሆነውን ውሃ ያውቃሉ የገሊላ ክፍል በምትሆን በቃና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የደረገው የተአምራቱ መጀመሪያ ይህ ነው ሦስት ዓመት ከ3 ወር ከሚያደርገው ተአምራት የሚቀድም አንድም ደገኛ/ታላቁ/ ተአምራት ይህ ነው። ተአምራቱንም ያደረገው በሀልዮ ነው።

<u>አንድም</u> በሦስተኛው ቀን ሠርግ ተደረገ ማለት በሦስተኛው ክፍለ ዘመን ሥጋዌ ተደረገ።እናቱ ማለት የባሕርይ ጥበቡ ከሥጋዌ አስቀድሞ ነበረች ስቴ ሕይወት ስቴ መድኃኒት ባለቀባቸው ጊዜ የባሕርይ ጥበቡ ተሰቅዬ ስቴ ሕይወት ስቴ መድኃኒት ልሁንላቸው አስኘችው። ነገር ግን የምሰቀልበት ጊዜ አልደረሰም ጌታ የሚሰቀል በአራተኛው ፋሲካ ነውና።

ስድስት የደንጊያ ጋኖች በ6ኛው ሺ የነበረ ሰው ሁሉ አእምሮው እንደ ደንጊያ መፍዘዙን መናገር ነው። የመጀመሪያው ወይን የኦሪት፣ ጠጅ የሆነው ውሃ/2ኛው ወይን/ የወንጌል ምሳሌ ነው።

## <u>አንጽሖተ ቤተመቅደስ</u>

አይሁድ ፋሲካን የሚየከብሩበት ቀን ደረሰ መጀመሪያ ፋሲካ ነው ጌታ የሚሰቀለው በአራተኛው ፋሲካ ነውና። ዮሐንስ ፋሲካውን ጠንቅቆ ይጽፋል። ጌታችን ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ። በመቅደስ ላም፣ በግ፣ ርግብ፣ የሚሸጡትን አገኘ ቤተ መቅደሱን ገበያ አድርገውት አገኘ። በጅራፍ ላሙን በጉን ሁሉ ከምኩራብ አስወጣ ማለት ገበያውን ፈታ። የለዋጮቹን ገንዘባቸውን በተነባቸው። ርግብ የሚሸጡትንም ወንበራቸውን ገለበጠባቸው በአባቴ ቤት ገበያ አታድርጉ። ደቀመዛሙርቱም የቤትህ ቅናት አቃጠለኝ የሚል ጽሑፍ እንዳለ አሰቡ። ገበያ መፍታት ማን ሥልጣን ሰጠህ አሉት። ጌታችንም ይህን ቤተመቅደስ አፍርሱት በሦስተኛው ቀን አንጸዋለሁ አላቸው። አይሁድም ይህ ቤተመቅደስ በ46 ዓመት ተሠርቶ ነበር። አንተ ግን በሦስተኛው ቀን አንጸዋለሁ አልክ።

እሱ ግን መቅደስ ስለሚባል ሰውነቱ እንዲህ አላቸው መቅደስ ስለሚባል ሰውነቱ እንደሆነ ዐወቁ።

<u>አንድም</u> ጌታ ወደ ኢየሩሳሌም ወጥቶ ተሰቀለ መሥዋዕተ ኦሪትን፣ ሥርዓተ ኦሪትን በሥልጣነ ክህነትተክቶ አሳለፈ።በአባቴ ቤት መሥዋዕተ ኦሪት አትሠዉ።ይህን ቤተመቅደስ አፍርሱት በሦስተኛው ቀን አንጸዋለሁ ማለት በመስቀል ተሰቅዬ ሞቼ በሦስተኛው ቀን እነሣለሁ ሲል ነው።



CS CamScanner

## ምዕራፍ ሦስት

## ጌታና ኒቆዲሞስ

ካመኑት ከፈሪሳውያን ወገን ከብዙዎቹ አንዱ ኒቆዲሞስ የሚባል የአይሁድ አለቃ ነበር **አለቅነቱ**፦ በትምህርት፣ በሹመት፣ በሀብት/በባለ ጸግነት ነው። **አስቀድሞ በሌሊት** ወደ ጌታ የመጣ ማለት ከግንዘቱ አስቀድሞ የመጣ አንድም በመዓልት ከሚመጡት አስቀድሞ የመጣ አንድም ከማመን አስቀድሞ አንድም ውዳሴ ከንቱ ሽቶ አንድም የሌሊት ልብ ክት ነውና ትምህርት እንዲረዳው አንድም አይሁድን ስለፈራ በአጠቃላይ ከግላ ኦሪት እንዳልተላቀቀ በመንፈስ ቅዱስ እንዳልተማወቀ ያጠይቃል።

ከእግዚአብሔር ተልከህ ልታስተምር እንደመጣህ እናውቃለን ያለማመን አባባል ነው አንድም ከእግዚአብሔር አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ ተወልደህ ልታስተምር እንደመጣህ እናውቃለን። እግዚአብሔር በህልውናው ከእርሱ ጋር ካለህ በስተቀር

### ዳግም ልደት

ጌታ ዳግመኛ ያልተወለደ ሃይማኖትን/መንግሥተ ሰማያትን አያውቃትም ብዬ በእውነት እነግራችኋለሁ። ኒቆዲሞስም ሰው ካደገ በኋላ ሁለተኛ መውለድ እንደምን ይቻላል አለው እንደገና ወደ አባቱ አብራክ ወደ እናቱ ማኅፀን መግባት ይቻለዋልን

ልደቱን ተናግሮ መወለጃውን አልተናገረም ነበርና ሁለተኛ ከአብራክ መንፈስ ቅዱስ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ ካልተወለደ መንግሥተ ሰማያት መግባት አይቻለውም ብዬ እነግርሃለሁ አለው። እማይ ብሎ ወልድን፣ እመንፈስ ቅዱስ ብሎ መንፈስ ቅዱስን እግዚአብሔር ብሎ እግዚአብሔር አብን ጠቀሰው።

ከግዙፍ ሥጋ የተወለደ ግዙፍ ነው ከረቂቅ መንፈስ ቅዱስ የምትወለድ ነፍስ ረቂቅ ናትና። ነፋስ ወደወደደው ይነፍሳል ድምፁን ትሰማዋለህ የሚመጣበት የሚሄድበትን አታውቅም። ከመንፈስ ቅዱስ የሚወለዱት ልደት እንዲህ ነው። አንድም መንፈስ ረድኤት በወደደው ያድራል ትንቢት ሲያናገር ሱባኤ ሲያስቆጥር ትሰማዋለህ ሀብተ ሙሴ በኢያሱ ሀብተ ኤልያስ በኤልሳዕ ሲያድር አታውቅም።

ምድራዊ ልደታችሁን ስነግራችሁ/ብነግራችሁ ያልተቀበላችሁኝ ሰማያዊ ልደታችሁን ብነግራችሁ እንደምን ትቀበሉኛላችሁ ለዚህ ምክንያት አለው በጥምቀት በንፋሐት ይሰጣል ለዚያ ግን ንቃሕ መዋቲ/ዘትነውም ባለው ምክንያት የለውምና (ትንሣኤን ዳግም ልደት ሲል) አንድም ምድራዊ ልደቱን ስነግራችሁ ያልተቀበላችሁኝ ሰማያዊ ልደቱን ብነግራችሁ እንደምን ትቀበላላችሁ

## በናስ የተሠራው እባብ (አርዌ ብርት)

እስራኤል በምድረ በዳ ሳሉ ነዘር እባብ እየተነሣ ይፈጃቸው ነበር ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ቢያመለክት ጽሩዩን ብርት እባብ አስመስለህ ሠርተህ ከሚገናኙበት አደባባይ ላይ ስቀልላቸው ያልጸናባቸው መልኩን አይተው የጸናባቸው ድምጹን ሰምተው የሚድኑ ሆነዋል። ሙሴ በምድረ በዳ እባቡን እንደሰቀለ የሰው ልጅ ክርስቶስ ይሰቀል ዘንድ አለው። አርዌ ምድር የዲያብሎስ አርዌ ብርት የጌታ ምሳሌ ነው። አርዌ ብርት በአርዌ ምድር (የናስ እባብ በምድር እባብ) አምሳል መስቀሉ ጌታም በአርአያ ጊጉያን (በደለኛ አምሳል) ለመሰቀሉ ምሳሌ ተጉለቆ ምስለ ጊጉያን እንዲል መልኩን አይተው ድምጹን ሰምተው የዳኑ ከቃሉ ሰምተው የዳኑ ሲሆኑ ድምጹን ብቻ ሰምተው የዳኑ ከእርሱ በኋላ ከተነሡ መምህራን ሰምተው የዳኑ የምእመናን ምሳሌ በእርሱ ያመነ ሁሉ ለዘለዓለም ይድናል እንጂ አይጎዳም። አንድ ልጁን ለሁሉ ቤዛ አድርጎ እስከመስጠት ደርሶ እግዚአብሔር ሰውን ወዶታልና በእርሱ ያመነ አይፈረድበትም። በአንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስላመነ በእርሱ ባለመነ ግን ይፈረድበታል።

ወዘእግዚአብሔር ፈነዎ ቃለ እግዚአብሔር ይናገር እግዚአብሔር የሾመው እውነተኛ መምህርም የእግዚአብሔርን ነገር ያስተምራል። እግዚአብሔር ሰጪነት ተከፍሎበት ሀብተ መንፈስ ቅዱስ በልክ የሚሰጠው አይደለም።

አብ ልጁን ይወደዋልና ሁሉን በእጁ ጭብጥ በእግሩ እርግጥ አድርጎ አስገዛለት። ዘየአምን በወልድ ቦ ሕይወት በወልድ ያመነ የዘለዓለም ሕይወት አለው። በወልድ ያላመነ ግን የማታልፍ መንግሥተ ሰማያትን አይወርስም።



CS CamScanner